# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በትምህርት ሚኒስቴር በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የውጤት ተኮር ስልጠና እና የቴክኖሎጂ ሽግግርና ክምችት ስርአት ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ
## የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2004ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ሥልጣንና ተግባር ........ 2
የስትራቴጂው ዝርዝር ዓላማዎች ........ 3
የዘርፉ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ........ 4
የፋይናንስ ምንጭ ........ 4
የኦዲቱ ዓላማ ........ 4
የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ........ 5
ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (potential audit area) ........ 5
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (audit issues) ........ 5
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria) ........ 6
የሥራ ሂደት መግለጫ ........ 7
የተቋማት አመራር ብቃት ስርዓት መዘርጋት ........ 10
ክፍል ሁለት ........ 14
ግኝቶች ........ 14
ሀ. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተቋማት አቅም ግንባታና ........ 14
የሰልጣኞች ልማት የስራ አፈፃፀም በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ........ 14
መከናወኑን በተመለከተ፡፡ ........ 14
የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስልጠና ፍላጎት ማጥናታቸውን በተመለከተ.. 14
የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናትን በተመለከተ ........ 15
በተቋማቶቹ የተሟላ የስልጠና መስጫ መሳሪያ አቅርቦት መኖሩን በተመለከተ ........ 16
የትብብርና ግንኙነት (clustering) ስርዓትን በተመለከተ ........ 17
የውጤት ተኮር ስልጠና ያለበትን ደረጃ በተመለከተ ........ 18
ተቋማት የድህረ ገበያ ጥናት ማከናወናቸውን በተመለከተ ........ 19
የሰልጣኞች የስልጠና ጊዜ 70% ቱን በኢንደስትሪው 30% ቱን ደግሞ በተቋማት ትግበራ መከናወኑን በተመለከተ ........ 21
በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መደገፉን በተመለከተ ........ 23
ለ. የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ስርዓት ኢኮኖሚያዊና ........ 24
ብቃት ባለው መልኩ መከናወኑን በተመለከተ፣ ........ 24
የምርጥ ቴክኖሎጂ የመለየት የመምረጥ እና የማሸጋገር ስራን በተመለከተ ........ 24
በቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር አሰራር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መስራቱን በተመለከተ ........ 25
የማሰልጠኛ ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገላቸውን በተመለከተ ........ 27
የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የአካባቢውን የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና መስራታቸውን በተመለከተ ........ 29
ተቋማት ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር የሚያገለግሉ መረጃዎችን በአግባቡ የሚይዙበት እና ስራ ላይ የሚያውሉበት የመረጃ አያያዝ ስርአት መዘርጋታቸውን በተመለከተ ........ 31
ቴክኖሎጂ ማምረት ሂደት ወቅት የወጡ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን መመዝገባቸውን በተመለከተ ........ 33
የቴክኖሎጅ ሽግግር ቅንጅታዊ አሠራርን በተመለከተ ........ 34
ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር ስራ የሚውሉ ማንዋሎችና መመሪያዎችን በተመለከተ፣ ........ 36
ተቋማትና ኮሌጆች የደሰሳ ጥናት ስለማድረጋቸው የሚደረገውን ክትትል በተመለከተ ........ 37
የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት መካሄዱን በተመለከተ ........ 38
ክፍል ሶስት ........ 40
መደምደሚያ ........ 40
ክፍል አራት ........ 43
የማሻሻያ ሀሳብ ........ 43
አባሪ 1 ........ 1

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና በተለያየ ደረጃ ቀደም ባሉት ዓመታት ወጥነት በሌለው መልኩ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ አገሪቱ በተለያዩ ሙያዎች የሠለጠኑ የቴክኒክ ባለሙያዎች እንደሚያስፈልጓትና በዚህ ረገድ የሚሰጠው የሥልጠና ኘሮግራም ኋላቀርና ካለው የስራ ሁኔታ ጋር ያልተዛመደ መሆኑን በመረዳት መንግሥት ከ1980ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓትን ለማሻሻል ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ጀመሯል፡፡
2. በዚሁም መሠረት ከ1989 እስከ 1998 ዓ.ም ባሉት አመታት ግብርና ነክ ያልሆኑ መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጡ ተቋማት ቁጥር ከ17 ወደ 199 ያደገ ሲሆን የተማሪዎች ቁጥርም በተመሳሳይ ጊዜ ከ3000 ወደ 106,300 ከፍ ብሏል፡፡ ከነዚሁ ውስጥ 31 በመቶ ያህሉ የሰለጠኑት መንግስታዊ ባልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ነው፡፡
3. መንግሥት በ1992 ዓ.ም አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስትራቴጂ ያወጣ ሲሆን ይህንኑም መሠረት በማድረግ በ1994 ዓ.ም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አዋጅ አውጥቷል፡፡ በ1996 ዓ.ም የተነደፈው የትምህርት ዘርፍ ልማት ኘሮግራም Educational Sector Development Program (ESDP) III የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ዘርፉን አጠቃላይ የዕድገት ራዕይ አስቀምጧል፡፡ በተደረገው የዘርፉ ትንተና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚጠብቁትንና የሚፈልጉትን በመካከለኛ ደረጃ የሠለጠነ የሰው ኃይል የሚያፈሩ ሆነው ባለመገኘታቸው በውጤት ላይ የተመሠረተና ገበያ ተኮር የሆነ፣ ጥናዊና አምዳዊ ተያያዥነት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ስርዓት መዘርጋት እንደሚገባ አስቀምጧል፡፡ በዚሁ መሠረት በ1996 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 391/96 የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና አዋጅ ወጥቷል፡፡

## የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ሥልጣንና ተግባር

4. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ በአዋጅ ቁጥር 391/1996 መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡

- ❖ የሀገሪቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስትራቴጅ ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ያስፈፅማል፣
- ❖ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ልማትና እድገት ስትራቴጅ መሰረት በማድረግ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናዎችን ይወስናል፣
- ❖ የመካከለኛ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች የሚደራጁበትን የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣል፣ የሙያ ስልጠና ደረጃንና ስርአተ ትምህርት ያዘጋጃል፣ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣
- ❖ የማሰልጠኛ ተቋማት የሚመሩበትና እውቅና የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚወስኑ መመሪያዎችን ያወጣል፣አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፣
- ❖ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ስርአትን ያደራጃል፣ይቆጣጠራል፣
- ❖ ሀገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማጠናቀቂያ ማስረጃ አሰጣጥ መመሪያ ያወጣል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣
- ❖ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች ከሀገሪቱ የልማት ትልምና የሰው ሀይል ፍላጎት ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እየተካሄዱ ስለመሆናቸው ጥናትና ክትትል ያደርጋል፣
- ❖ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዙሪያ ምርምሮች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣
- ❖ የስራ ላይ ልምምድ አፈፃፀም መመሪያዎችን ያወጣል፣ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣
- ❖ የስልጠና ፕሮግራሞችን ውጤታማነትና ስኬታማነትን ለማረጋገጥ የድህረ ስልጠና ክትትል እንዲካሄድ ያደርጋል፣
- ❖ የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች ስኬታማ እንዲሆኑ እገዛ ያደርጋል፣
- ❖ የግል ባለሀብቶች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የሚሳተፉበትን መንገድ ያመቻቻል፣
- ❖ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ሴቶች ፣አካል ጉዳተኞች እንዲሁም ታዳጊ ክልሎች ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ የሚያስችል ስርአት ይቀይሳል፣
- ❖ የካውንስሉ ሴክሬታሪያት በመሆን ያገለግላል፣

- ❖ የፅሕፈት ቤቱን የስራ እቅድና በጀት ያዘጋጃል ሲፀድቅም በስራ ላይ ያውላል፣
- ❖ ከካዉንስሉ ሰብሳቢ ጋር በመመካከር የካውንስሉን የስራ እቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ለካውንስሉ የተፈቀደለትን በጀት ያስተዳድራል፡፡

5. መንግስት ለቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ትኩረት በመስጠት በ1999 ዓ.ም አገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ስትራቴጂ አውጥቷል፡፡ የስትራቴጂው ዋና ዓላማ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች ፍላጎት ላይ የተመሠረተና ከፍተኛ ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና መስጠት ነው፡፡

## የስትራቴጂው ዝርዝር ዓላማዎች

- ❖ ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል የሚሆኑበትን አሠራር ማጠናከር፣
- ❖ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን /መደበኛውንና መደበኛ ያልሆነውን/ ጥራት በሁሉም ደረጃ ማሻሻልና ከስራ ገበያው ፍላጎት ጋር ማጣጣም፣
- ❖ የተቀናጀ የተዋሃደ፣ በውጤት ላይ የተመሠረተና ያልተማከለ ስርአትን መፍጠርና ማጠናከር፣
- ❖ ለአገር እድገት ቁልፍ ሚና ባላቸው የስራ መስኮች ላይ ትኩረት በማድረግ አግባብነት ያለው ስልጠና የሚሰጥበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- ❖ ለሁሉም ተዋናዩችና ባለድርሻዎች የተቀናጀ የአሠራር ማዕቀፍ መፍጠርና ኢንዱስትሪውም በስልጠናው ላይ በሰፊው እንዲሳተፍ ማበረታታት፣
- ❖ በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን በብቃት ለመምራት ተገቢውን ተቋማዊ አደረጃጀትና አስፈላጊውን ብቁ የሰው ኃይል አቅም መገንባት፣
- ❖ ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢና ዘለቄታ ያለው የፋይናንስ ስርዓትና የሥራ አመራር መዋቅር መዘርጋት፣
- ❖ ሴቶችንና የገጠሩን ነዋሪ ህዝብ እንዲሁም ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ወገኖች የሙያ ክህሎት ባለቤት በማድረግ በራሳቸው ጉዳይ ተስሚነታቸውን ማጠናከርና እኩል የተሳትፎ እድል ማግኘታቸውን ማረጋገጥ የሚሉት ናቸው፡፡

## የዘርፉ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

6. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ በአንድ ሚኒስትር ዴኤታ ሲመራ ለሚኒስትር ዴኤታው ተጠሪ የሆኑ ሶስት ዳይሬክቶሬቶች (ውጤት ተኮር ስልጠና ዳይሬክቶሬት፣ የሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና ዳይሬክቶሬት፣ የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ዳይሬክቶሬት) ይገኛሉ፡፡ የመምህራን ልማት ቡድን፣የሰልጣኞች ልማት ቡድን እና የተቋማት አቅም ግንባታ ቡድን በውጤት ተኮር ስልጠና ዳይሬክቶሬት ስር የሚገኙ ሲሆን፤የሙያ ደረጃ ምደባ ቡድን እና የሙያ ብቃት ምዘና ቡድን በሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና ዳይሬክቶሬት ስር ይገኛሉ፡፡ በነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር የሰው ሀይል አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በተገኘው መረጃ መሰረት ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ 52 የሰው ሀይል የሚያስፈልግ ቢሆንም በስራ ላይ የሚገኙት ግን 33 ሰራተኞች ብቻ ናቸው፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

7. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ የፋይናንስ ምንጩ የፌዴራል መንግስቱ ከሚመድብለት ዓመታዊ በጀትና ከእርዳታ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በ2002 በጀት ዓመት ለካፒታል በጀት ከግምጃ ቤት ብር 50,002,000 ተመድቦ ብር 20,505,974 (41%) ስራ ላይ ዉሏል፡፡በ2003 በጀት ዓመት ብር 48,834,850.89 ተመድቦ ብር 36,558,752.16 (74.86%) ስራ ላይ የዋለ ሲሆን የመደበኛ በጀቱ የሚዘጋጀው በጥቅል የቴክኒክና ሙያ፣ የአጠቃላይ ትምህርት እና የከፍተኛ ትምህርት በመሆኑ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተመደበውን ለይቶ ማወቅ አልተቻለም፡፡

## የኦዲቱ ዓላማ

8. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የቴክኖሎጅ ሽግግርና ክምችት እና የውጤት ተኮር ስልጠና ስርአትን በመገምገም በአሰራር ላይ በታዩ ድክመቶች የማሻሻያ ሀሳቦችን በመስጠት አሰራሩ እንዲሻሻል ለማድረግ ሲሆን ይህም በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነት ከመወጣት ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው፡፡

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

9. ኦዲቱ የሸፈነው ከ2001 እስከ 2003 በጀት አመት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተከናወነውን ስራ ነው፡፡ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ሆኖ በኦሮሚያ ቴክኒክና ሙያ ኮሚሽን እና በስሩ በሚገኙ በናሙና የተመረጡ በ 5 ተቋማትና ኮሌጆች፣ በአማራ የቴክኒክና ሙያ ቢሮ እና በስሩ የሚገኙ 9 ኮሌጆችና ተቋማት እንዲሁም በአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲና በስሩ በሚገኙ በአራት /4/ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችና ተቋማትን ያካተተ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ለኦዲቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በመከለስ፣ የመስክ ጉብኝት በማካሄድና ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለመጠይቅ በማድረግ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (potential audit area)

10. ከላይ የተጠቀሰውን የኦዲት ዘዴ በመጠቀም የኦዲት ቡድኑ ሁለት የኦዲት አካባቢዎችን መርጧል፡- እነርሱም፡-

I. በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ የሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና ስርአት ውጤታመነቱን መገምገም እና፣

II. በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ የቴክኖሎጅ ሽግግርና ክምችት እና የውጤት ተኮር ስልጠና ስርዓት ውጤታማነቱን መገምገም

የሚሉት ሲሆኑ በስጋት ትንተና የመምረጫ መስፈርት መሰረት ብልጫ ያገኘው በተራ ቁጥር ሁለት የተጠቀሰው የኦዲት አካባቢ ተመርጧል፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (audit issues)

11. ከላይ የተመለከተውን የኦዲት ዓላማ ለማሳካት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (audit issues) ተመርጠዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. **በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ የቴክኖሎጅ ሽግግርና ክምችት ስርአት መዘርጋቱን፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ እና ብቃት ባለው ሁኔታ መከናዎኑን መገምገም፣**

2. **በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ የተቋማት አቅም ግንባታና የሰልጣኞች ልማት አፈፃፀም መገምገም፣**

   2.1. **የተቋማት አቅም ግንባታ ስራ በብቃት መከናዎኑን መገምገም፣**

   2.2. **በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የሰልጣኞች ልማት**

እንቅስቃሴ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፣

ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative Criteria)

*12.* ከላይ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ለመመዘን የሚረዱ 29 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅቷል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

# የሥራ ሂደት መግለጫ

## የሙያ ደረጃ ምደባና ብቃት ምዘና ዋና የስራ ሂደት

### ሀ. የሙያ ደረጃ ምደባ ንዑስ የስራ ሂደት

### የሙያ ደረጃ ምደባ ስርዓት መዘርጋት

13. ስለ ሙያ ደረጃ መመሪያ አዘገጃጀት የሌሎች አገሮችን ልምድ በመዳሰስ የስርዓቱን መመሪያ በማዘጋጀትና በማሻሻል ተጠቃሚዎችን በማብቃት መመሪያው እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡

### ሙያዎች መለየት

14. በየዘርፉ ተባባሪ (ቀጣሪ) መስሪያ ቤቶችን በመለየትና ግንኙነት በመፍጠር የአገሪቱ የልማት ስትራቴጅዎችና ፖሊሲዎችን በመመርመር የየዘርፉን የሰለጠነ የሰው ሃይል ፍላጎት የሚያሳይ መነሻ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡የሙያ አይነቶችን ለሚለዩ ባለድርሻ ድርጅቶች፣ የሙያ ማህበራት፣ ወዘተ ጥሪ በማስተላለፍና ባለሙያ ስለመመደባቸው በማረጋገጥ በአውደ ጥናት የሙያ ዓይነቶችን በመለየት የአውደጥናቱን ውጤት ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በማስወሰን ለሙያ ደረጃ ምደባ ዝግጁ ያደርጋል፡፡

### የሙያ ደረጃ ማዘጋጀት

15. በሙያ ደረጃ ዝግጅት የሚሳተፉ ድርጅቶችን በመለየትና ግንኙነት በመፍጠር የሙያ ደረጃ ዝግጅት የሚካሄድበት ቦታ፣ ጊዜ እንዲሁም ግብዓትና በጀት ይወስናል፡፡በሙያ ደረጃ ዝግጅት ላይ ለሚሳተፉ ድርጅቶች ጥሪ በማስተላለፍ፣ባለሙያ ስለመመደባቸው በማረጋገጥ እና ለሙያ ደረጃ ዝግጅት የሚረዳ ምርጥ ተሞክሮ (Benchmark) በማሰባሰብና ለአውደጥናት ግብዓት በሚውል መልክ በማደራጀት የሙያ ደረጃ ዝግጅት ዓውደ ጥናት በማካሄድ (ስለውጤት-ተኮር ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጣና ስትራተጂ ገለፃ ይደረጋል፣ ስለ ሙያ ደረጃ ጠቀሜታ ማስረዳትና በአዘገጃጀቱ ላይ ተግባራዊ ሥልጠና ይሰጣል) የሙያ ደረጃ ምደባ ይከናወናል፡፡የተዘጋጀውን የሙያ ደረጃ ምደባ ኤዲት በማድረግ የተዘጋጀው የሙያ ደረጃ ይፀድቃል፡፡

## የሙያ ደረጃ ሰነዶችን ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት

16. የፀደቁ የሙያ ደረጃ ሰነዶችን በሲዲ በማዘጋጀት ያሰራጫል በዌብሳይት ላይም እንዲጫን (upload) ይደረጋል፡፡

## የሙያ ደረጃ ምደባና ስርጭት ግምገማ ማካሄድ

17. መረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች በማዘጋጀት መረጃ (ግብረ-መልስ) ይሰበሰባል፡፡ የተሰባሰቡ መረጃዎችን በማጠናቀር ውጤቱን ለየተግባራቱ አፈፃፀም ማሻሻያ በሚውል መልኩ ይቀመራል፡፡

## ለ. የሙያ ብቃት ምዘና ንዑስ የስራ ሂደት

## የሙያ ብቃት ምዘና ስርዓት መዘርጋት

18. የሙያ ብቃት ምዘናና ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ፣የምዘና መሳሪያ አዘገጃጀት ማንዋል፣የመዛኞች ስልጠናና ዕውቅና ማንዋል፣የምዘና ማዕከላት ዕውቅና አሰጣጥ ማንዋል በማዘጋጀት በተዘጋጁ መመሪያዎች ላይ የፈጻሚዎችን አቅም በመገንባት የመመሪያውንና ማኑዋሎችን ትግበራ ላይ ክትትልና ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## የሙያ ብቃት ምዘና መሳሪያ ማዘጋጀት

የተዘጋጁ የሙያ ደረጃዎችን በማሰባሰብ እና ለሙያ ምዘና መሳሪያ ዝግጅት ዓለምአቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማሰባሰብ ከኢንደስትሪው ጋር በመሆን የወርክሾፕ ተሳታፊዎችን በመለየትና በመጋበዝ የወርክሾፕ ተሳታፊዎችን (የኢንደስትሪ ኤክስፐሮቶችን) በምዘና መሳሪያዎች ዝግጅት ላይ ስልጠና ይሰጣል፡፡የሙያ ምዘና መሳሪያዎችን ከተዘጋጀው የሙያ ደረጃ ጋር በኢንዱስትሪው ባለሙያዎች ተሳትፎ አጣጥሞ ያዘጋጃል፡፡

በአውደ ጥናት የተዘጋጁ የምዘና መሳሪያዎችን በማስተካከል የሙያ ምዘና መሳሪያዎችን ያሰራጫል በምዘና ግብረ መልስ መሰረትም ጥቅም ላይ የዋሉ የሙያ ምዘና መሳሪያዎች ላይ ማሻሻያ ያደርጋል፡፡

## መዛኞችን ማሰልጠንና ዕውቅና መስጠት

19. የመዛኞች ስልጠና ለማካሄድ ዝርዝር እቅድ በማዘጋጀት በመመሪያው መሰረት በሙያ ብቃት ምዘና ላይ የሚሳተፉ ባለሙያዎች መምረጫ መስፈርት ያዘጋጃል፡፡በመዛኝነት ስልጠና የሚሳተፉ ባለሙያዎችን በመስፈርቱ መሰረት በመምረጥና በመጋበዝ የመዛኝነት

ስልጠና በመስጠት ዕጩዎች ይለያል፡ ዕጩዎችን በመዛኝነት በማሳተፍ ብቃት ላላቸው ዕውቅና ይሰጣል፡፡ዕውቅና ለተሰጣቸውም መዛኞች ተከታታይ (refresher) ስልጠና ይሰጣል፡፡

## የምዘና ሂደቱን መከታተልና መገምገም

20. ለክትትልና ግምገማ መስፈርት በማዘጋጀት በክትትልና ግምገማ መስፈርቱ ላይ ግንዛቤ ለፈጻሚዎች እና ለምዘና ማዕከላት ኃላፊዎች በምዘና አሰጣጥ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር በመስፈርቱ መሰረት የምዘና ሂደቱን ይገመግማል ለታዩ ችግሮችም የማስተካከያ መፍትሄዎች በማስቀመጥ ለፈፃሚዎች እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

## የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት

21. የብቁ ተመዛኞችን መረጃ በማሰባሰብ ፣ የምስክር ወረቀት ህትመት በማመቻቸት እና የምዘናውን ውጤት ትክክለኛነት በማረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ምሥክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## የምዘና መረጃ ባንክ ማደራጀትና መጠቀም

22. የምዘና መረጃ ባንክ ንድፍ በማዘጋጀት የምዘና መረጃ በመሰብሰብ ፣በማደራጀት፣ የተሰበሰበውን መረጃ ወደ ዳታ ባንክ በማስገባት እና በመተንተን ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ በግብረ መልሱም መሰረት በአሰራር ላይ ማሻሻያ ይደረጋል፡፡

## የሙያ ብቃት ምዘና ግምገማ ማካሄድ

23. መረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች በማዘጋጀት መረጃ (ግብረ-መልስ) ይሰበሰባል የተሰባሰቡ መረጃዎችንም በማጠናቀር ውጤቱን ለየተግባራቱ አፈፃፀም ማሻሻያ በሚውል መልኩ ያዘጋጃል፡፡

## የውጤት ተኮር ስልጠና ዋና ስራ ሂደት

## ሀ. የመምህራን ልማት ንዑስ የስራ ሂደት

## የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና መምህራን ብቃት ማዕቀፍ ስርዓት መዘርጋት

24. የመምህራን ብቃት ማዕቀፍ ሰነድ በማዘጋጀት በተዘጋጀው ብቃት ማዕቀፍ ሰነድ ላይ የክልሎችን አቅም በመገንባት በብቃት ማዕቀፍ ስርዓቱ አተገባበር ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## የቅድመ ስራ ስልጠናና ብቃት ማረጋገጫ ስርዓት መዘርጋት

25. የቅድመ ስራ ስልጠናና ብቃት ማረጋገጫ ስርአት ሰነድ በማዘጋጀት በተዘጋጀው ስርዓት ሰነድ ላይ የክልሎችን አቅም በመገንባት በብቃት ማረጋገጫ ስርዓቱአተገባበር ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስርዓት መዘርጋት

26. የሙያ ማሻሻያ ስርአት ሰነድ በማዘጋጀት በተዘጋጀው ስርዓት ሰነድ ላይ የክልሎችን አቅም በመገንባት በሙያ ማሻሻያ ስርዓቱ አተገባበር ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል ፡፡

## የመምህራን ልማት ተግባራት ግምገማ ማካሄድ

27. መረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች በማዘጋጀት መረጃ (ግብረ-መልስ) ይሰበሰባል፡፡ የተሰባሰቡ መረጃዎችን በማጠናቀር ውጤቱን ለየተግባራቱ አፈፃፀም ማሻሻያ በሚውል መልኩ ይዘጋጃል፡፡

## ለ. የተቋማት አቅም ግንባታ ንዑስ የስራ ሂደት

## የተቋማት አመራር ብቃት ስርዓት መዘርጋት

28. የተቋማት አመራር ብቃት ስርዓት ሰነድ በማዘጋጀት በተዘጋጀው ብቃት ስርዓት ሰነድ ላይ የክልሎችን አቅም በመገንባት በብቃት ስርዓቱ አተገባበር ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## የተቋማት ውጤታማ ሀብት አጠቃቀምና የጥራት ማኔጅመንት ስርዓት መዘርጋት

29. የተቋማት ሀብት ውጤታማ አጠቃቀምና ጥራት ማኔጅመንት ስርኣት ሰነድ በማዘጋጀት በተዘጋጀው ስርአት ሰነድ ላይ የክልሎችን አቅም በመገንባት በተቋማት ሃብት አጠቃቀም ስርዓት ስራ ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ምርጥ ተሞክሮዎችን በመዳሰስ የተቋማት የሃብት አጠቃቀምና ጥራት ማኔጅመንት አማራጭ በማቅረብ ያስፈፅማል፡፡

## የተቋማት ማስፋፋት ስርዓት መዘርጋት

30. የተቋማት ማስፋፋት ሰነድ በማዘጋጀት በተቋማት ማስፋፋት ስርዓት ሰነዱ ላይ የክልሎችን አቅም በመገንባት በተቋማት ማስፋፋት ስራ ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

*የተቋማት ብቃት ማረጋገጫ ስርዓት መዘርጋት*

31. የተቋማት ብቃት ደረጃ ሰነድ በማዘጋጀት በተዘጋጀው ብቃት ደረጃ ሰነድ ላይ የክልሎችን አቅም በመገንባት በተቋማት ብቃት ማረጋገጫ ስርአት አተገባበር ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ምርጥ ተሞክሮዎችንም በመዳሰስ በተቋማት ብቃት ስርዓት ላይ አማራጭ ይቀርፃል፡፡

*የተቋማት አቅም ግንባታ ተግባራት ግምገማ ማካሄድ*

32. መረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች በማዘጋጀት መረጃ (ግብረ-መልስ) በማሰባሰብ፣ የተሰባሰቡ መረጃዎችን በማጠናቀር ውጤቱን ለየተግባራቱ አፈፃፀም ማሻሻያ በሚውል መልኩ ያዘጋጃል፡፡

## ሐ. የሰልጣኞች ልማት ንዑስ የስራ ሂደት

*የስራ ገበያ ፍላጎት ዳሰሳ ስርዓት መዘርጋትና ሀገራዊ የስራ ገበያ ፍላጎት ጥናት ማከናወን*

33. የስራ ገበያ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማንዋል በማዘጋጀት በስራ ገበያ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ለክልሎች አቅም በመገንባት በጥናቱ ሂደት ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

*በስርዓት ትምህርትና የማስተማሪያ ማሰልጠኛ መማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ስርዓት መዘርጋት*

34. በስርዓት ትምህርት፤ የማስተማሪያ ማሰልጠኛ መማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ማንዋል በማዘጋጀት በስርዓት ትምህርት፤ የማስተማሪያ ማሰልጠኛ መማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ላይ የክልሎችን አቅም በመገንባት የስርዓት ትምህርት፤ የማስተማሪያ ማሰልጠኛ መማሪያ መሳሪያዎች አተገባበርን ይገመግማል ማሻሻያም ያደርጋል፡፡

*የትብብር፣ የኩባንያ ውስጥ፣ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ የአሰለጣጠን ስርዓት መዘርጋት*

35. የትብብር፤ የኩባንያ ውስጥ፣ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ስልጠና ስርዓት በመቅረጽ/በማሻሻል የትብብር፤ ኩባንያ ውስጥ፣ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ስልጠና ስርዓት ማንዋል ያዘጋጃል፡፡ በስርዓቱ ላይ የክልሎችን አቅም በመገንባትና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመዳሰስ በአሰለጣጠን ዘዴዎች/ስልቶች ላይ አማራጭ በማቅረብ የትብብር፤ ኩባንያ ውስጥ፣ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ስልጠና ላይ ግንዛቤ ይፈጠራል፡፡በአተገባበሩም ላይ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

### የሰልጣኞች ምክርና ድጋፍ አገልግሎት ስርዓት መዘርጋት

36. የሰልጣኞች ምክርና ድጋፍ አገልግሎት ማንዋል በማዘጋጀት በማንዋሉ ላይ የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት የሰልጣኞች ምክርና ድጋፍ አገልግሎት አተገባበር ላይ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

### የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማት የማደራጀትና የማብቃት ስርዓት መዘርጋት

37. የስርዓት ሰነድ በማዘጋጀት በተዘጋጀው ሰነድ ላይ የክልሎችን አቅም በመገንባት የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማት የማደራጀትና የማብቃት ሂደት ላይ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡

### የስልጠና ፋይዳ ግምገማ ማካሄድ

38. የስልጠና ፋይዳ ግምገማ ማኑዋልና የመገምገሚያ መሳሪያ በማዘጋጀት በማኑዋሉና መገምገሚያ መሳሪያው ላይ የክልሎችን አቅም በመገንባት የስልጠና ፋይዳ ግምገማ ይካሄዳል፡፡የግምገማውን ውጤት ለስርዓቱ ማሻሻያነት እንዲውልም ያዘጋጃል፡፡

## የቴክኖሎጅ ሽግግር ዋና ስራ ሂደት

### የቴክኖሎጂ ሽግግር ስርዓት መዘርጋት

39. አለማቀፍ ተሞክሮዎችን በመፈተሽ ረቂቅ ስርዓቱን በመንደፍ እና ከባለድርሻዎች ጋር በመወያየት በስርዓት ሰነዱ ላይ ለፈጻሚዎች የአቅም ግንባታ ስራ በማከናወን የእሴት ሰንሰለት ትንተና መመሪያ ያዘጋጃል፡፡

### ለተለዩት ኢንዱስትሪዎች የእሴት ሰንሰለት ትንተና ስርዓት መዘርጋትና ትንተና ማካሄድ

40. መመሪያው ስራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ ግንዛቤ በመፍጠርና ከልማት ስትራቴጂው በመነሳት ወሳኝ የልማት ዘርፎችን ግቦች ይለያል፡፡ በተለዩት ወሳኝ የልማት ዘርፎች ውስጥ የሚገኙ ኢንዲስትሪዎችና ግቦቻቸውን በመለየትና የእሴት ሰንሰለት መግለጫ (Value Chain Mapping) ተግባር ይሰራል፡፡ በእሴት ሰንሰለት መግለጫ (Mapping) መሰረት ችግሮችን መለየትና በክብደት ቅደም ተከተላቸው በማስቀመጥ የእሴት ሰንሰለት መግለጫ ተግባራት ላይ ክትትልና ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## የምርጥ ቴክኖሎጂ ፍላጎት የመለየትና የመምረጥ ስርዓት መዘርጋትና የቴክኖሎጂ ምርጫ ማከናወን

41. የምርጥ ቴክኖሎጂ ፍላጎት የመለየትና የመምረጥ መመሪያ በማዘጋጀት በመመሪያው አፈጻጸም ላይ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ የምርጥ አሰራር የመለየት ተግባር ያከናወናል፣ ለችግሮቹ መንስኤ በሆነው አሰራርና በምርጡ አሰራር መካከል ያለውን ክፍተት በመለየትና የመምረጫ መስፈርት በማዘጋጀት ክፍተቱን የሚሞላ ምርጥ ቴክኖሎጂ በመለየት ቴክኖሎጂውን ይመረጣል፡፡የተመረጠውን ቴክኖሎጂ በማግኘትና ለተቋማት መረጃውን በማስተላለፍ የምርጥ ቴክኖሎጂ ፍላጎት የመለየትና የመምረጥ ተግባራትን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## ምርጥ ቴክኖሎጂ የማከማቸት ስርዓት መዘርጋት

42. የምርጥ ቴክኖሎጂ የማከማቸት (የመስሪያ ዝርዝር ሰነድ (Blue print) እና ቴክኖሎጂን የመቅዳት (Prototype)) አሰራር በመመሪያው አፈጻጸም ላይ አቅም በመፍጠር የምርጥ ቴክኖሎጂ ሽግግር ስርዓት መመሪያ ያዘጋጃል፡፡

## የምርጥ ቴክኖሎጂ ሽግግር ስርዓት መዘርጋት

43. ምርጥ ቴክኖሎጂ የማከማቸት ተግባራትን በመከታተልና ድጋፍ በመስጠት በመመሪያው አፈጻጸም ላይ አቅም በመፍጠር የምርጥ ቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራትን ይከታተላል ድጋፍም ይሰጣል፡፡

## የተሸጋገረ ቴክኖሎጂን ፋይዳ ዳሰሳ ማካሄድ

44. መረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች በማዘጋጀት መረጃ (ግብረ-መልስ) በማሰባሰብ የተሰባሰቡ መረጃዎችን በማጠናቀር ውጤቱን ለየተግባራቱ አፈፃፀም ማሻሻያ በሚውል መልኩ ያዘጋጃል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

## ሀ. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተቋማት አቅም ግንባታና የሰልጣኞች ልማት የስራ አፈፃፀም በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን በተመለከተ፡፡

### የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስልጠና ፍላጎት ማጥናታቸውን በተመለከተ

44. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስልጠና ፍላጎት በማጥናት ለክልል የቴክኒክና ሙያ አስፈጻሚ አካላት በየአመቱ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

45. በአማራ ክልል የሚገኙት በአዲስ ዘመን፣ ደንበጫ፣ እንጅባራ እና በኦሮሚያ ክልል በሚገኙት የጅማ፣ ጊምቢ፣ ቴፒ፣ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሃላፊዎች የሰልጣኞች የስልጠና ፍላጎት ጥናት መጠናቱን ቢገልጹም መረጃውን ለኦዲት ቡድኑ ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡ በሌላ በኩል በአማራ ክልል በአዴት፣ ደጀን፣ ደብረ ማርቆስ፣ ዳንግላ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ዱርቤቴ፣ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በዳበና፣ በነቀምት፣ አምቦ፣ በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙት የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት መካከል በአቃቂ፣ ከፍተኛ 12፣ ከፍተኛ20 ተቋማት ኃላፊዎች የሰልጣኞች የስልጠና ፍላጎት ጥናት እንደማይካሄድ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በአዲስ አበባ መስተዳድር የሚገኙት የግል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋሞች ውስጥ በአዲስ አበባ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅና ዩንቨርሳል ቴክኖሎጂ ኮሌጅ ጥናቱን እንዳላካሄዱ የኦዲት ቡድኑ ለኃላፊዎቹ ባቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

46. ስለጉዳዩ የኦሮሚያ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው ተቋማቱ በገበያ ፍላጎት እንጂ በሰልጣኞች ፍላጎት መሰረት እንደማይሰሩ ገልፀዋል፡፡

47. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስልጠና ፍላጎት ጥናት አለማካሄዳቸው በማሠልጠኛ ተቋማት የሚሰጠው ስልጠና የሰልጣኞችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ስለማይሆን የሚሰጠው ስልጠና ውጤታማ ላያደርገው ይችላል፡፡

## የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናትን በተመለከተ

48. በትምህርት ሚኒስቴር በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ፣ በክልል ቢሮዎች እንዲሁም በማሰልጠኛ ተቋማትና ኮሌጆች የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናት በማጥናት ስልጠናውን በጥናቱ መሠረት ማካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡

49. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በኦሮሚያና በአማራ ቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች ስር በሚገኙ ተቋማትና ኮሌጆች የስራ ገበያ ፍላጎት ጥናት የሚያጠኑ ቢሆንም ስልጠናው የሚሰጠው ግን በጥናቱ መሠረት ሳይሆን የክልሉ የቴክኒክና ሙያ ቢሮ ለማሰልጠኛ ተቋማት በሚልከው የሰልጣኞች የስልጠና መስፈርት መሆኑን የሥራ ኃላፊዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

50. ጉዳዩን በተመለከተ ለኦሮሚያና አማራ ቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች የሥራ ኃላፊዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የሥራ ገበያ ፍላጎት በክልል ደረጃ የሚጠና ቢሆንም በተቋማት የሚጠናው ጥናት በሕብረተሰቡ እና በተቋማት ማህበረሰብ በስልጠና ዘርፎችና በሙያ ደረጃዎች ላይ ያለው ግንዛቤ አናሣ በመሆኑ ምክንያት በተቋማት የሚጠናው ጥናት ከቢሮዎቹ ጥናትና ከአገሪቱ የትኩረት አቅጣጫ ጋር ሊሄድ እንዳልቻለ ገልፀዋል፡፡

51. በአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ ስር በሚገኙ የከፍተኛ 20፣ ከፍተኛ 12፣ አቃቂ እና ብርሃን ኢትዮጵያ ተቋማትና ኮሌጆች የአካባቢያቸውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት ያደረገ የገበያ ጥናት እንደማያጠኑ ለሥራ ኃላፊዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ በተቋማቱና ኮሌጆች የሚሰጠው ስልጠና ኤጀንሲው በሚያጠናው የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናት መሠረት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

52. ጉዳዩን በተመለከተ በትምህርት ሚኒስቴር በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የውጤት ተኮር ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ በቀረበው ቃለ መጠየቅ አገር አቀፍ የስራ ገበያ ፍላጎት እንደሚያጠኑና ክልሎችና የማሰልጠኛ ተቋማት የአገር አቀፍን ጥናት መሠረት በማድረግ እንደየአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናት ማጥናት እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

53. የሥራ ገበያ ፍላጎት እንደየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ አለመጠናቱ ከማሰልጠኛ ተቋማት ስልጥነው የሚመረቁ ሰልጣኞች የሥራ እድል በአካባቢያቸው እንዳያገኙ ከማድረጉም በላይ የሥልጠና ዘርፎች ቀጣይነት ላይ የጐላ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

## በየተቋማቶቹ የተሟላ የስልጠና መስጫ መሳሪያ  አቅርቦት መኖሩን በተመለከተ

54. የክልል ቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች የአገር አቀፍ ሙያ ደረጃን የሚያሟላ ስልጠና ለመስጠት በየተቋማቶቹ የተሟላ የስልጠና መስጫ መሳሪያዎች መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

55. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በአማራ ክልል በሚገኙ የዱርቤቴ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ዳንግላ፣ እንጅባራ፣ ደብረ ማርቆስ፣ ደጀን፣ አዴት፣ አዲስ ዘመን እና ደንበጫ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፡ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ጅማ፣ ነቀምት፣ ጊምቢ፣ አምቦ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እንዲሁም በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር በሚገኙት ከፍተኛ 12፣ ከፍተኛ20፣ አቃቂ፣ ብርሃን ኢትዮጵያ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሙያ ደረጃው የሚጠይቀውን የተሟላ ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል የስልጠና መሳሪያዎች አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለተቋማቱ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅና የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የመስክ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡

56. የተቋማቱ የስራ ኃላፊዎች ለችግሩ መሠረታዊ ምክንያቶች ናቸው ብለው የገለጹት ተከታታይ የሆነ የክትትል እጥረት፣ የክልል እና የፌደራል ድጋፍ አናሳ መሆኑ፣ የመንግስት የግዥ ስርአት አስቸጋሪ መሆኑ እና በየአመቱ የካሪኩለም መለዋወጥ ለችግሩ አለመቀረፍ ምክንያት እንደሆኑ ለኦዲት ቡድኑ አስረድተዋል፡፡

57. ስለጉዳዩ ለአማራ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ኃላፊ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እንደገለፁት እስከ አሁን ባለው ሁኔታ በተለይ አዳዲስ ተቋማት ላይ ያልተሟሉ መሆኑንና ችግሩንም ለመቅረፍ በጀት በመመደብ በ125 ሚሊየን ብር መሳሪያዎችን በመግዛት ወደ አገር ውስጥ እየገባ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

58. በተመሳሳይ መልኩ የኦሮሚያ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ኃላፊ እንደገለፁት የማቴሪያል እጥረት እንዳለ የሚታወቅ ቢሆንም ይህንን ክፍተት ለመፍታት በትብብር ስልጠና እንዲታገዝ እንደሚደረግ ነገር ግን ኢንዱስትሪዎች ሠልጣኞችን ያለመቀበል ችግር እንዳለ ገልፀዋል፡፡

59. ጉዳዩን በሚመለከት በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና  ዘርፍ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊ በቀረበላቸው ቃለ

መጠይቅ በሰጡት መልስ ከአጋር ድርጅቶች ሀብት የማፈላለግ ተግባር በስፋት ቢሰራም ለሁሉም ተቋማት ማዳረስ አለመቻሉን እና ችግሩ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

60. በተቋማቶቹ የተሟላ የትምህርት አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎች አቅርቦት አለመኖሩ ሰልጣኞች በሚሰለጥኑበት የሙያ ደረጃ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዳይጨብጡ በማድረግ በተለይ የተግባር ስልጠናው ላይ የጎላ ተፅእኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

## <u>የትብብርና ግንኙነት (clustering) ስርዓትን በተመለከተ</u>

61. የክልል የቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች በስራቸው ለሚገኙ ተቋማት የስራ ትብብርና ግንኙነት (clustering) ስርዓት በመዘርጋት ተቋማት እርስ በርሳቸው በቅንጅት የሚሰሩበት የስምምነት ሰነድ እንዲኖራቸው ማድረግና መከታተል ይጠበቅባቸዋል፡፡

62. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት ክልሎች በአማራ፣ ኦሮሚያና የአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የስራ ትብብርና ግንኙነት (clustering) ስርአት የተዘረጋ ቢሆንም የስራ አፈጻጸሙ ያልተጠናከረና ተቋሟቱም በቅንጅት የሚሰሩበት የትብብር ሰነድ እንደሌላቸው በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

63. በአማራ ክልል ከሚገኙት የቴክኒክና ሙያ ተቋማት መካከል የዱርቤቴ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ዳንግላ፣ እንጅባራ፣ ደብረ ማርቆስ፣ ደጀን፣ አዴት፣ አዲስ ዘመን እና በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ ተቋማት መካከል የአምቦ፣ ጊምቢ፣ ነቀምቴ፣ ደበና፣ ጂማ የስራ ትብብርና ግንኙነት (clustering) ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም የሚጠበቀው የልምድ ልውውጥ በተጠናከረ መልኩ እንዳልተካሄደ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር በሚገኙ ብርሀን ኢትዮጵያ፣ አቃቂ፣ ከፍተኛ 20፣ ከፍተኛ12 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስራ ትብብርና ግንኙነት (clustering) ስርዓቱ በእቅድ ደረጃ የተዘጋጀ እንደሆነ በኦዲቱ ወቅት ለተቋማቱ የስራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የማሠልጠኛ ተቋማትና ኮሌጆች እርስ በርሳቸው በቅንጅት የሚሠሩበት የስምምነት ሰነድ እንዳልተዘጋጀ የኦዲት ቡድኑ ለስራ ኃላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ገልፀዋል፡፡

64. በተመሳሳይ መልኩ በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ የግል ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ማለትም ዩንቨርሳል ቴክኖሎጂ ኮሌጅና አዲስ አበባ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የስራ ትብብርና ግንኙነት (clustering) ስርዓቱ የተዘጋጀ ቢሆንም በተጠናከረ ሁኔታ እየተሰራ

እንዳልሆነ፡ እንዲሁም በዩንቨርሳል ቴክኖሎጅ ኮሌጅ የስምምነት ሰነድ ቢዘጋጅም ተግባራዊ አለመደረጉን፡ በአዲስ አበባ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የስምምነት ሰነድ በእቅድ ደረጃ ተይዞ ለማዘጋጀት መታቀዱን የመሳሪያ ልውውጥም አለመከናወኑን ለተቋማቶቹ ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት መልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡

65. ስለ ጉዳዩ የኦሮሚያ እና አማራ ቴክኒክና ሙያ ቢሮ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በተቋማት አቅም ግንባታ ከታዩት ችግሮች የክላስተር መሪ ተቋማት ሌሎች ተቋማትን በተሟላ መልኩ ለማብቃት አለመስራታቸውን እና የስምምነት ሰነድ እንዳልተዘጋጀም ገልፀዋል፡፡

66. ጉዳዩን በሚመለከት በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በፌደራልና በክልል የቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች የሚደረገው ክትትል አጥጋቢ አለመሆኑ፣የአመለካከት ችግር፣ ተቋማት ተደራጅተው ያለመስራትና መልካም ተሞክሮዎችን ለማሰራጨት አለመቻል የስራ ትብብርና ግንኙነት (clustering) ስርዓቱና እርስ በርሳቸው በቅንጅት የሚሰሩበት የስምምነት ሰነድ አዘጋጅተው በተጠናከረ ሁኔታ እንዳይሰራ እንዳደረገ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በስልጠና ስኬታማነት ላይ ያለውን ፋይዳ በአግባቡ አለመረዳት የችግሩ መንስኤ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

67. የስራ ትብብርና ግንኙነት (clustering) ስርዓቱ የተዘረጋ ቢሆንም በተጠናከረ ሁኔታ እየተሰራ አለመሆኑና የስምምነት ሰነድ አለመዘጋጀቱ በተቋማት መካከል መደረግ ያለበት የማቴሪያል፣ የሰው ኃይል ልውውጥና የእውቀት ሽግግር እንዳይጠናከር ያደርገዋል፡፡

## የውጤት ተኮር ስልጠና ያለበትን ደረጃ በተመለከተ

68. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍና የክልል ቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች የልህቀት ማእከል center of competency (coc) ውጤትን መሰረት በማድረግ የውጤት ተኮር ስልጠና ያለበትን ደረጃ መገምገም ይኖርባቸዋል፡፡

69. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት የክልል ቴክኒክና ሙያ ኤጀናሲዎች መካከል የአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች እንደገለጹት ብዙዎቹ ተቋማት ያላስመዘኑ መሆናቸውን ገልጸው በእንጦጦ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና

ኮሌጅ ግን የአለፈውን አመት ተሞክሮ ተግባራዊ በማድረግ ለሠልጣኞች ተቋማዊ ምዘና በመስጠት ያለፉትን የብቃት ምዘና በማስፈተን 30% ያህል ያሳለፈ ሲሆን ይህንን ተሞክሮ በሌሎች ተቋማት ለማስፋት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሁለት ጊዜ እንደሰጡ ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል የአማራና የኦሮሚያ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ቢሮ ኃላፊዎች እንደገለጹት የልህቀት ማዕከልን (coc) ውጤት መሰረት በማድረግ የውጤት ተኮር ያለበትን ደረጃ የሚገመግምበት ስልት መኖሩን ገልፀው ግምገማውንም በክልል ደረጃ በኦሮሚያ በ2003 26%ቱ በአማራ 28%ቱ ከተፈተኑ ሰልጣኞች ውጤታማ እንደሆኑ ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡ በሌላ መልኩ በቀሪዎቹ ሰልጣኞች ላይ ያለባቸውን የእውቀት፣ የክህሎትና የአመለካከት ችግሮችን በመለየት ወደፊት ሰልጣኞች በስልጠና እያሉ በቂ የስልጠና ክህሎት ማግኘት እንዳለባቸው ገልፀዋል፡

70. የውጤት ተኮር ስልጠና ያለበትን ደረጃ በተመለከተ በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ ለውጤት ተኮር ዳይሬክቶሬት የሥራ ኃላፊ በቀረበው ቃለ መጠየቅ በሰጡት መልስ ከልህቀት ማዕከል (coc) መረጃዎችን በመውሰድ የውጤት ተኮር ስልጠና ያለበትን ደረጀ እንዳልተገመገመ ገልፀዋል፡፡ ግምገማው ያልተካሄደበት ምክንያት ለሥራው በቂ የተደራጀ የሰው ኃይል ያለመኖርና ሥራውን ከፌዴራል አስከተቋማት ተቀናጅቶ ያለመሰራቱ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

71. የልህቀት ማእከል (coc) ዉጤትን መሰረት በማድረግ የውጤት ተኮር ስልጠና ያለበትን ደረጃ አለመገምገም የስልጠናውን የጥራት ደረጃ ለመገምገም ካላማስቻሉም በተጨማሪ ኢንዱስትሪው በሚፈልገው የሙያ ብቃት ባለሙያዎችን ለማፍራት አያስችልም፡፡

## ተቋማት የድህረ ገበያ ጥናት ማከናወናቸውን በተመለከተ

72. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሰልጠነው የተመረቁ ሰልጣኞች ከስልጠና በኋላ የትና በምን ሥራ ላይ እንዳሉ የድህረ ገበያ ጥናት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

73. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት በአማራ፣ ኦሮሚያና አዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሰልጣኞቻቸው ከስልጠና በኋላ የትና በምን ስራ ላይ እንዳሉ አብዛኞቹ ተቋማት የድህረ ገበያ ጥናት እንደማያካሂዱ ታውቋል፡፡

74. በአማራ ክልል የሚገኙት አዲስ ዘመን፣ አዴት፣ ደጀን፣ ደብረ ማርቆስ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ዳንግላ፣ የዱርቤቴ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሰልጥነው የተመረቁ ሰልጣኞች ከስልጠና በኃላ የትና በምን ስራ ላይ እንዳሉ የድህረ ገበያ ጥናት በየአመቱ ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ በሰልጣኞች አድራሻ እና ተቋሙ በሚያዘጋጀው ቅፅ መሰረት ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን ቢገልፁም የተጠናቀረውን መረጃ የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ለማቅረብ አልቻሉም፡፡ በሌላ መልኩ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ጂማ፣ ደበና፣ ነቀምት፣ ጊምቢ፣ ሰልጥነው የተመረቁ ሰልጣኞች ከስልጠና በኃላ የትና በምን ስራ ላይ እንዳሉ የድህረ ገበያ ጥናት እንደማይከናወን፡ ለኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር በሚገኙ ከፍተኛ 20፣ ከፍተኛ 12፣ ብርሀን ኢትዮጵያ፣ አቃቂ ተቋማትና አዲስ አበባ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ሰልጥነው የተመረቁ ሰልጣኞች ከስልጠና በኋላ የትና በምን ስራ ላይ እንዳሉ የድህረ ገበያ ጥናት በተጠናከረ መልኩ እንደማይከናወን በኦዲቱ ወቅት ለኃላፊዎቹ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡

75. ጉዳዩን በሚመለከት በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ስራው በጅምር ቢኖርም ተቋማት የጋራ እቅድ አዘጋጅተው ስለማይነሱ የድህረ ገበያ ጥናት ለማካሄድ እንዳልቻሉ ገልፀው ከዚህ በተጨማሪ ተቋማት ከኢንዱስትሪው ጋር አብሮ የመስራት ችግር መኖሩ፣ የሚሰጠው የአቅም ግንባታ አናሳ መሆኑና የክትትል ስራው አናሳ መሆን የድህረ ገበያ ጥናት ላለማካሄድ ምክንያት መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

76. ሰልጥነው የተመረቁ ሰልጣኞች ከስልጠና በኃላ የትና በምን ስራ ላይ እንዳሉ የድህረ ገበያ ጥናት በተጠናከረ መልኩ አለመከናዎኑ ስልጠናው በትክክል ገበያው በሚፈልገው የሙያ አይነት እየተከናወነ መሆኑን ለመገምገምና ሰልጣኞችም በሰለጠኑበት የሙያ አይነት ስራ ማግኘታቸውን በመከታተል በተቋሙ የስልጠና መርሀ ግብር ላይ ማሻሻያ ለማድረግ አያስችልም፡፡

## የሰልጣኞች የስልጠና ጊዜ 70% ቱን በኢንደስትሪው 30% ቱን ደግሞ በተቋማት ትግበራ መከናወኑን በተመለከተ

77. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሰልጣኞች የስልጠና ጊዜያቸውን 70% ቱን በኢንደስትሪ ውስጥ በተግባር ልምምድ 30%ቱን ደግሞ በንድፈ ሃሣብ ስልጠና እንዲያሳልፉ ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

78. በአማራ ክልል ስር በሚገኙ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት መካከል በፍኖተ ሰላም፡ ዱርቤቴ፣ ዳንግላ፣ እንጅባራ፣ አዴት፣ ደንበጫ፣ አዲስ ዘመን እና ደጀን ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በኢንደስትሪ የተግባር ስልጠናው በተቀመጠው ፐርሰንት አለመሰራቱን በኦዲቱ ወቅት የተቋማቶቹ የስራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ገልፀዋል፡፡ የትብብር ስልጠናውን የሚሰጡት ኢንደስትሪዎች ግንዛቤ አናሳ መሆኑ፣ የአመለካከት ችግር፣ የተሟላ ወርክ ሾፕ አለመኖሩ፣ መሳሪያዎች አለመሟላታቸው የትብብር ስልጠናውን ለመስጠት ያለው የቁጥጥርና ድጋፍ በተጠናከረ መልኩ አለመከናወኑ የትብብር ስልጠናው በተሳካ ሁኔታ እንዳይከናወን ያደረጉ ምክንያቶች መሆናቸውን የስራ ኃላፊዎች አያይዘው ገልፀዋል፡፡

79. በደብረ ማርቆስ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ሰልጣኞች በአብዛኛው የሚያልፉት በተግባር ስልጠና ቢሆንም የኩባንያ ውስጥ ስልጠናን ለመስጠት በቂ ኢንደስትሪ አለመኖሩና የባለሙያ እጥረት መኖሩ፣ የአመለካከት ችግር መኖሩ፣ ለሰልጣኞች በሙሉ እምነት እቃዎችን አምኖ አለመስጠት የመሳሰሉ ችግሮች መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

80. በደቡብ ክልል የቴፒ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም የተቀመጠውን ፐርሰንት ለማስፈፀም ከቴፒ ዩኒቨርሲቲ፣ ከውሀ ልማት መ/ቤት፣ እና ከጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ጋር በመተባበር እየተሰራ ቢሆንም ተግባራዊነቱ እንደተፈለገው ያህል አለመሄዱን ኃላፊው በኦዲቱ ወቅት በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ገልፀዋል፡፡

81. በኦሮሚያ ክልል በጊምቢ እና በጅማ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በአካባቢው በቂ ኢንደስትሪዎች አለመኖራቸው፣ የተሟሉ መሳሪያዎች አለመኖሩ እና የተግባር ስልጠናው በተሟላ መልኩ እየተከናወነ አለመሆኑን ለኃላፊዎቹ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ገልፀዋል፡፡

82. በአምቦ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋም ስልጣኞች በብዛት የተግባር ስልጠና እንዲያገኙ መምህሩ አብሮ ኩባንያው ድረስ በመሄድ ስልጠናው በትክክል መሰጠቱን እንደሚያረጋግጥ እና የኢንደስትሪ ፎረም በ 2003 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ ግንዛቤ ቢፈጠርም የኢንደስትሪዎች እጥረት በመኖሩ ስራው በበቂ ሁኔታ እንዳልተሰራ ኃላፊው ገልፀዋል፡፡

83. በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር በሚገኙ ከፍተኛ 12፣ ብርሀን ኢትዮጵያ፣ አቃቂ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት እና ዩኒቨርሳል ቴክኖሎጅ ኮሌጅ እና አዲስ አበባ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በትብብር ስልጠና ኢንደስትሪዎች ሰልጣኞችን የመቀበል ፍላጎት የሌላቸው በመሆኑ ስልጠናው በተሟላ መልኩ እየተሰጠ እንዳልሆነ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

84. የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የዶክመንት ክለሳ በ2003 በጀት አመት የትብብር ወይም የኩባንያ ውስጥ ስልጠና በመንግስት ተቋማት ከሚሰለጥኑ ሰልጣኞች ውስጥ 239,864 (50%) የሚሆኑት በትብብር ስልጠና እንዲሰለጥኑ በእቅድ ተይዞ እየሰለጠኑ ካሉት 303,951 ውስጥ 118,467 (39%) የሚሆኑት በትብብር ስልጠና እንደታቀፉና ለአፈፃፀም ዝቅተኝነትም ዋናው ምክንያት ተቋማት ሰልጣኞችን ለአንድ ሳምንት ወደ ኢንደስትሪ በመላክ የትብብር ስልጠና እንደተካሄደ አድርጎ መቁጠር፣ አመራሩም ሆነ መምህሩ የትብብር ስልጠና አተገባበር መርሆዎች ላይ በቂ ግንዛቤ በመጨበጥ አለመምራትና አለመተግበር እና የአመለካከት ችግር (የትብብር ስልጠና በተቋም አመራር እየተመራ አለመሆኑ) እንደሆኑ ከትምህርት ሚኒስቴር የ2003 በጀት አመት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የትብብር ስልጠና ብቃት ያለው ባለሙያ መፍለቂያ፣ የብቁ አሰልጣኝ ማፍሪያ እና የመምህራን እጥረት መፍቻ መንገድ አድርጎ አለመወሰድ ሀገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስትራቴጅ አፈፃፀም ግምገማና የ2003 ዓ.ም.የህዝብ ንቅናቄ መፍጠሪያ እቅድ ላይ ተገልጿል፡፡ በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና ተግባር ተኮር ከማድረግ ይልቅ ንድፈ ሀሳባዊ ማድረጋቸውን የ2003 ዓ.ም የውጤት ተኮር ስልጠና አፈፃፀም ግምገማ መረጃ ላይ ተገልጿል፡፡

85. ጉዳዩን በሚመለከት በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የትብብር ስልጠናው በተጠናከረ መልኩ ያለመሰራቱ ምክንያት የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባር በስፋት አለመሰራቱና በኢንደስትሪውና በቴክኒክና ሙያ

ትምህርትና ስልጠና አመራሮች የአመለካከት ችግሮች በመኖሩ መሆኑን ኃላፊው ገልፀዋል፡፡

86. ሰልጣኞች 70%ቱን የስልጠና ጊዜ በኢንደስትሪው (በትብብር የተግባር ስልጠና) በተሟላ መልኩ አለማግኘታቸው ከስልጠና በኋላ ወደ ተግባር ሲገቡ አስፈላጊውን ክህሎት እንዳይጨብጡ በስራም ላይ ውጤታማ እንዳይሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

## በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መደገፉን በተመለከተ

87.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ እና የቴክኒክ እና ሙያ ቢሮዎች በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለመደገፍ የሚያስችል ስልት በመቀየስ ተግባራዊነቱን መከታተል ይኖርባቸዋል፡፡

88.በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በሚገኙ ጅማ፣ ዳበና፣ ነቀምት፣ ጊምቢ እና አምቦ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በበቂ የኢንፎርሚሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች እንዳልተደገፉ በኦዲቱ ወቅት ለተቋማቱ የስራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

89.በኦሮሚያ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እንደገለፁት በተቋማት የሚሰጡ ስልጠናዎች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ በበቂ ሁኔታ ተደግፈው እንደማይሰጡ ገልፀዋል፡፡

90.በአዲስ አበባ በሚገኙት በከፍተኛ 20 ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ያሉት ኮምፒውተሮች የዱሮ መሆናቸውና አዲስ የሆኑትን ሶፍት ዌሮች መቀበል አለመቻሉን በኦዲቱ ወቅት ለስራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡ በሌላ መልኩ በከፍተኛ 12 እና በብርሀን ኢትዮጵያ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ በአዲስ አበባ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና ዩኒቨርሳል ቴክኖሎጅ ኮሌጅ ደግሞ የሚሰጠው ስልጠና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተደግፎ እንደሚሰጥ የስራ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

91.ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የመረጃ ክለሳ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ለሚሰሯቸው ስራዎችና ለሚያደርጓቸው ግንኙነቶች አስፈላጊ የሆኑ ዘመናዊ የቴክኖሎጅ መሳሪያዎች (ኮምፒውተር፣ኢንተርነት) እንዳልተሟሉ በትምህርት ሚኒስቴር የ2003 በጀት አመት የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ተገልጿል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአማራ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ለኃላፊው በቀረበላቸው ቃለ

መጠይቅ እንደገለፁት የውጤት ተኮር ስልጠና በተቀናጀ መልኩ የሚሰጥ ሲሆን ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂም በሁሉም መስኮች እንደሚሰጥ ገልፀዋል፡፡

92. ጉዳዩን በሚመለከት በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በሙያው ፕሮፌሽናል ባለሙያ አለመኖሩ፣ የግብአት አለመሟላት (የአቅም ውስንነት) በስልጠናው ጥራት ላይ ተፅእኖ እንዳስከተለ ኃላፊው ገልፀዋል፡፡

93. በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ በበቂ ሁኔታ የማይደገፍ ከሆነ በሰልጣኞች ላይ የክህሎት ክፍተት በመፍጠር ሁለገብ የሆነ እውቀት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡

# ለ. <u>የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ስርዓት ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው መልኩ መከናወኑን በተመለከተ፣</u>

## <u>የምርጥ ቴክኖሎጂ የመለየት የመምረጥ እና የማሸጋገር ስራን በተመለከተ</u>

94. በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የምርጥ ቴክኖሎጂ ፍላጎት በመለየት እና በመምረጥ ቴክኖሎጂዎች እንዲሸጋገሩ ለማድረግ መረጃውን ወደ ተቋማትና ኮሌጆች በመላክ አፈጻጸሙን ሊከታተልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

95. በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ እና በክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ የምርጥ ቴክኖሎጂ ፍላጎት የመለየት፣ የመምረጥ እና የማከማቸት ስርአት የተዘረጋ ቢሆንም በኦዲት ቡድኑ በናሙና ከተመረጡት በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ እና በአዲስ አበባ ስር በሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ቴክኖሎጂ እንዲሸጋገር በፌደራልም ሆነ በክልል የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ አነስተኛ መሆኑን የተቋማትና የኮሌጆች የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

96. ጉዳዩን በተመለከተ ለአማራ፣ ለኦሮሚያና ለአዲስ አበባ የቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ የስራ ሀላፊዎች የኦዲት ቡድኑ ባቀረበው ቃለ መጠይቅ ስራው ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ የተጀመረ በመሆኑ፣ በሰው ሀይል እጥረት፡ መዋቅሩ አዲስ በመሆኑና በየጊዜው በመቀያየሩ ስራው በተፈለገው መጠን እንዳልተሰራ ገልፀዋል፡፡

97. የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን በተመለከተ በትምህርት ሚኒስቴር ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የስራ ሀላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ የቴክኖሎጂ ፍላጎት የመለየት፣ የመምረጥ እና የማከማቸት ስርአት ተዘርግቶ 12 ሚሊዮን የሚደርሱ የከለላ ጊዜያቸው ያለፈባቸው(patent free) ቴክኖሎጅዎችን በማሰባሰብ ለክልሎች እንደተሰራጨ ገልጸዋል፡፡ ስራው ከታች እስከ ላይ በትክክል ስለመፈጸሙ ዘርፉ ከክልሎች ጋር በየሶስት ወሩ በጋራ የምክክር መድረክና በናሙና በሚመረጡ ክልሎች ሱፐርቪዥን በማካሄድ ክትትል የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ስራው ከጫፍ እስከ ጫፍ የእሴት ሰንሰለት የመተንተን፣ ቴክኖሎጂን የመምረጥ፣ የተመረጡ ቴክኖሎጂዎች ንድፍ የመስራት የተሰሩ ንድፎችን መሰረት አድርጎ ናሙና የመስራትን ስራ ስለሚያጠቃልል በዘርፉ መንግስት ካስቀመጣቸው ከሰባቱ የኢንደስትሪ ትኩረት አቅጣጫ ውስጥ ከኮንስትራክሽን ዘርፍ በገጠር መንገድ በአስራ አንድ ቴክኖሎጂዎች ላይ ቢከናወንም በሌሎች ዘርፎች ላይ በሰው ሀይል በተሽከርካሪና በማቴሪያል እጥረት ምክንያት ስራው እንዳልተሰራ እና በቂ ክትትልና ድጋፍ እንዳልተደረገ ገልፀዋል፡፡

98. የምርጥ ቴክኖሎጂ ፍላጎት የመለየት ፣ የመምረጥ እና ቴክኖሎጂዎች እንዲሸጋገሩ መረጃውን ወደ ተቋማትና ኮሌጆች የመላኩ ስራ ከፌደራል እስከ ተቋማት ድረስ በመቀናጀት በተጠናከረ መልኩ አለመሰራቱ እና በፌደራልና በክልል የቴክኒክና ሙያ ባለሙያዎች በቂ ክትትል እና ድጋፍ አለመደረጉ የቴክኖሎጂ ሽግግሩ ስራ ውጤታማ እንዳይሆንና ተገቢውን የማሻሻያ ሀሳብም ለመስጠት አያስችልም፡፡

## በቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር አሰራር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መስራቱን በተመለከተ

99. በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ እና የክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮዎች ለማሰልጠኛ ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር አሰራር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

100. በናሙና በተመረጡ በኦሮሚያ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን ስር በሚገኙ በጅማ፣ ደበና፣ ነቀምት ፣ጊምቢ እና አምቦ ቴክኒክና ሙያ ተቋማትና ኮሌጆች ለተውጣጡ ባለሙያዎች በፌዴራልና በክልል የቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች በሚያዘጋጁት ስልጠናና በአመታዊ የቴክኖሎጂ ሳምንት የሚሳተፉ ቢሆንም በተግባር ላይ ያተኮረ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ለኮሌጆችም ሆነ ለተቋማት እንዳልተሰጠ ገልፀዋል፡፡

101. በናሙና በተመረጡ በአማራ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ስር በሚገኙ በደብረማርቆስ፣ አዲስ ዘመን እና እንጅባራ ቴክኒክና ሙያ ተቋማትና ኮሌጆች ለተውጣጡ ባለሙያዎች በፌዴራል እና በክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮዎች በሚዘጋጁ ስልጠናዎች እና ከሚላኩ መመሪያዎችና ሞዴሎች ውጭ በፌደራልም ሆነ በክልል የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ አስፈጻሚ አካላት በአካል በመገኘት ለተቋሙም ሆነ ለአካቢው ህብረተሰብ በቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር አሰራር ላይ በተግባር የተደገፈ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን አለመስራቱን ገልፀዋል፡፡ በሌላ መልኩ በደጀን፣ በፍኖተ ሰላም፣ በዳንግላ፣ በደንበጫ፣ ዱርቤቴና አዴት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ ምንም አይነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ከፌዴራልም ሆነ ከክልል ቢሮዎች እንዳላገኙ ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

102. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ስር በሚገኙ የቦንጋ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ እና የቴፒ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ በፌደራልም ሆነ በክልል የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ባለሙያዎች በአካል በመገኘት ለተቋሙም ሆነ ለአካባቢው ህብረተሰብ በቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር አሰራር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን አለመስራቱን የኦዲት ቡድኑ ለስራ ኃላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

103. በናሙና በተመረጡ በአዲስ አበባ ስር በሚገኙ የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ማለትም ከፍተኛ 20 እና ከፍተኛ 12 በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ ከተቋማቶቹ ለተውጣጡ ባለሙያዎች ስልጠና የተሰጡ ሲሆን በአቃቂ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅና ብርሃን ኢትዮጵያ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ስለ ቴክኖሎጅ ሽግግር ለተቋሙም ሆነ ለአካባቢው ህብረተሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን አለመስራቱን ገልፀዋል፡፡

104. የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን በተመለከተ ለአማራ፣ ለኦሮሚያ እና ለአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ የስራ ሀላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ ስለ ቴክኖሎጅ ሽግግር ለተቋሙም ሆነ ለአካባቢው ህብረተሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በኤግዚቢሽንና በሲምፖዝየም መልክ እየሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን በተለይ የማሰልጠኛ

ተቋማት ስራውን እንደመደበኛ ስራ አለመቁጠር፣ በሰው ሀይልና በማቴሪያል የአቅም ውስንነት  የሚሰጠውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የመተግበር ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ በቴክኖሎጅ ሽግግር ዙርያ  የሚሰሩ ስራዎች አጥጋቢ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

105. ጉዳዩን አስመልክቶ በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊ የኦዲት ቡድኑ ባቀረበው ቃለ መጠይቅ በፌደራል ደረጃ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የሚሰራው ስራውን በማስተባበር ረገድ ለሚያግዙ አካላት የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት ሲሆን ክልሎች ስራውን ወደ ህብረተሰቡ የማድረስና ሰነዶችን በአግባቡ የመተግበር ችግር እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ስራው በአግባቡ ላለመሰራቱ በተቋማትና ኮሌጆች ስራውን እንደተጨማሪ ስራ አድርጎ የመውሰድ ችግር እንዳለ ገልጸዋል፡፡

106. በማሰልጠኛ ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር አሰራር  ላይ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በፌዴራልና በክልል የቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች ባለመሰራቱ በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚሳተፉ ባለሙያዎች ስራውን እንደተጨማሪ ስራ አድርጎ የመውሰድና ለትምህርትና ስልጠናው ብቻ ትኩረት በመስጠት የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራን ወደ ጎን በመተው ስራውን በተፈለገው ፍጥነት እንዳይሰራ ያደርጋል፡፡

## የማሰልጠኛ ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገላቸውን በተመለከተ

107. የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገላቸውን መከታተልና መደገፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡

108. በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩት የኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ህዝቦችና የአዲስ አበባ መስተደድር ስር የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማትና ኮሌጆች የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል በመሆን እንዲያገለግሉ በክልል ቢሮዎች የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ የተለያየ የአፈጻጸም ደረጃ እንዳለው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በነባር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች ያለው አፈጻጸም የተሻለ ሲሆን በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ያለው አፈጻጸም ግን አጥጋቢ እንዳልሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

109. በናሙና ከተመረጡት በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ውስጥ አምቦ ተቋም፣ ጅማ ኮሌጅ፣ ጊምቢ ተቋም በክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን ተቋማቶቹ በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገላቸውን ክትትልና ድጋፍ

እንደማይደረግ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ስራው ላይ ለስራ ሀላፊዎቹ ባቀረበው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ችሏል፡፡ ይሁን እንጅ በነቀምት ኮሌጅ እና በደበና ኮሌጅ የክልሉ የቴክኒክና ሙያ ኮሚሽን ኮሌጆቹ በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገላቸውን ክትትልና ድጋፍ ማድረጉን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

110. በአማራ ክልል በሚገኙ እንጅባራ፣ ደንበጫ፣ ዳንግላ ፣ ደጀን፣ ፋኖተሰላም እና አዴት የክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ተቋማቶቹ በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገላቸውን ክትትልና ድጋፍ እንደማይደረግ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ስራው ላይ ለስራ ኃላፊዎቹ ባቀረበው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ችሏል፡፡ይሁን እንጅ በደብረማርቆስ ኮሌጅ፣ አዲስ ዘመን እና ዱርቤቴ ተቋም የክልሉ የቴክኒክና ሙያ ቢሮ ተቋማቶቹ በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገላቸውን ክትትልና ድጋፍ ማድረጉን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

111. በደቡብ ክልል በሚገኘው የቦንጋ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ የክልሉ ቴክኒክና ሙያ ቢሮ ኮሌጁ በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገላቸውን በበቂ ሁኔታም ባይሆን ክትትልና ድጋፍ ማድረጉን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ ለቴፒ ቴክኒክና ሙያ ተቋም የክልሉ ቢሮ ተቋሙ በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገሉን ክትትልና ድጋፍ እንደማይደረግ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

112. በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ ከፍተኛ 12፣ ከፍተኛ 20፣ ብርሃነ ኢትዮጵያ እና አቃቂ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ኤጀንሲው በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገላቸውን ክትትልና ድጋፍ እንደማይደረግ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

113. የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን በተመለከተ ለአማራ፣ ለኦሮሚያና አዲስ አበባ መስተደድር የቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ የስራ ሀላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እና በተደረገው የመስክ ስራ ጉብኝት በነባር ቴክኒክና ሙያ ተቋማትና ኮሌጆች የማሰልጠኛ ተቋማቶቹ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል መሆናቸውን በከፊል ክትትልና ድጋፍ በኤጀንሲው ቢደረግም በአዳዲሶች ተቋማት ላይ ተቋማቶች አዲስ በመሆናቸውና ገና በደንብ ያልተደራጁ ከመሆናቸው የተነሳ ስራውን ስለመስራታቸው የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ አነስተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

114. የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የመረጃ ክለሳ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ለኢንዱስትሪው የሰለጠነ የሰው ሀይል ከማቅረብ በተጨማሪ ምርጥ ቴክኖሎጂዎችን የሚያሸጋግሩና ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማትን በማደራጀት የሚያበቁ በመሆናቸው በዚህ ረገድ መኖር ያለበት የማደራጀትና ድጋፍ የመስጠት ስራ ተገቢው ግምት እንዳልተሰጠው በ2002 ዓም በተካሄደው የመሰረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ ጥናት ላይ ተገልጿል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከ2003-2007 በተዘጋጀው የትምህርት ዘርፍ ስትራቴጂ እቅድ ላይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ቴክኖሎጂን ለማሸጋገርና ለማስረጽ ብቁ ሆነው እንደማይገኙ ተገልጿል፡፡

115. የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገላቸውን የሚያደርጉት ክትትልና ድጋፍ አነስተኛ በመሆኑ በተለይ የማሰልጠኛ ተቋማት ከኮሌጆች በተለየ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል እንዲሆኑ በመንግስት የተቀረፀውን ስትራቴጂ በሚፈለገው ፍጥነት እንዳይሳካ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የአካባቢውን የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና መስራታቸውን በተመለከተ

116. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ኮሌጆች የአካባቢውን የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና /ማለትም የአንድን ለገበያ የሚቀረብ ምርት ከመጀመሪያ ጀምሮ አስከ ፍጆታ ድረስ ያሉና ለምርት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ነገሮች የሚቀነባበሩበት ዓላማ መር ቅደም ተከተል ስራ/ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

117. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ሕዝቦች እና የአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትና ኮሌጆች የአካባቢውን ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ስራ መስራታቸውን በተመለከተ የተለያየ የአፈጻጸም ደረጃ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

118. በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙት የአምቦ፣ ጊምቢ እና ደበና ተቋማት የአካባቢዉን የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና እንዳላካሄዱ ገልፀዋል፡፡ ያላካሄዱበትም ምክንያት በተቋማቶቹ የተደራጀ የሰው ሀይል ባለመኖሩና ለስራው በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩ ስራው እንዳልተሰራ ለሀላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ በነቀምትና ጅማ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የአካባቢውን

የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና ስራ እንደተሰራ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

119. በአማራ ክልል ውስጥ ከሚገኙ የደጀን፣ አዴት፣ ዳንግላ፣ ደንበጫ እና ፍኖተ ሰላም ተቋማት የአካባቢውን የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና እንዳላካሄዱ ታውቋል፡፡ የእሴት ሰንሰለት ትንተና ያላካሄዱበት ምክንያት ስለ እሴት ሰንሰለት ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆኑና ለስራው የተደራጀ የሰው ሀይል ባለመኖሩ መሆኑን የስራ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡ በሌላ መልኩ በደብረ ማርቆስ፣ እንጅባራ፣ ዱርቤቴና አዲስ ዘመን ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችና ተቋማት በተወሰኑ ቴክኖሎጂዎች የአካባቢውን የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና ስራ እንደተሰራ በኦዲቱ ወቅት ለሀላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

120. በደቡብ ክልል በሚገኘው የቦንጋ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ በተወሰኑ ቴክኖሎጅዎች ላይ የአካባቢውን የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና ስራ እንደተሰራ ለሀላፊው በቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ በቴፒ ቴክኒክና ሙያ ተቋም ስለ እሴት ሰንሰለት ምንም አይነት ግንዛቤ ባለመኖሩና በተቋሙ ስራውን የሚያስተባብር ባለሙያ ባለመኖሩ የአካባቢውን የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና ስራ እንዳልተሠራ ለሀላፊው በቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

121. በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር ከሚገኙ ተቋሞች ውስጥ ከአቃቂ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ በስተቀር ሌሎች ማለትም ከፍተኛ 12፣ ከፍተኛ 20 እና ብርሃን ኢትዮጵያ የአካባቢውን የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና ስራ እንደሚሰሩ የገለጹ ቢሆንም ለስራው በቂ ክህሎት ያለው የሰው ሀይል እና በጀት በማስፈለጉ ስራው የተፈለገውን ያህል እንዳልሄደ የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

122. ጉዳዩን በተመለከተ ለኦሮሚያ እና ለአማራ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ የስራ ሀላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ ምንም እንኳ ስራው የተቋማት ቢሆንም ቢሮዎቹ ከተቋማት ጎን ለጎን በአንዳንድ ቴክኖሎጂዎች ላይ የእሴት ሰንሰለት ትንተና ቢሰሩም መረጃው በተጠናከረ መልኩ ወደ ተቋማት እንዲወርድና ሁሉም ተቋማት ወደ ስራ እንዲሰማሩ የሚደረገው ድጋፍ በተለይ በተቋማት አነስተኛ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

123. ለአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ የስራ ሀላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ የእሴት ሰንሰለት ትንተና ስራ እስካሁን ያልተሰራ ሲሆን ወደፊት ስራውን በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ለመስራት ጅምሩ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

124. የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩን በተመለከተ በትምህርት ሚኒስቴር ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የስራ ሀላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ መንግስት ካስቀመጣቸው ከሰባቱ  የትኩረት ኢንዱስትሪዎች በተወሰኑት የእሴት ሰንሰለት ትንተና የተሰራ ቢሆንም በገጠር መንገድ ዘርፍ በተሰራው እሴት ሰንሰለት በመመርኮዝ 11 ቴክኖሎጅዎች መሰራታቸውንና በአብዛኛዎቹ ኢንዱስትሪዎች በሰው ሀይል አለመሟላት ምክንያት የሚጠበቀውን ያህል ስራ እንዳልተሰራ ገልፀዋል፡፡

125. በቴክኖሎጂ ፍላጎት መሰረት ቴክኖሎጂን የሚያሸጋግሩ ተቋማት የአካባቢዉን የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት ቴክኖሎጂው ለየትኛው አካባቢና ለምን ስራ እንደሚውል በመግለጽ፣ ቴክኖሎጂው ያለበትን ክፍተትና ጠቀሜታ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና በሁሉም ተቋማት አለመሠራቱ የሚሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎች የሚጠበቀውን ውጤት እንዳያመጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## <u>ተቋማት ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር የሚያገለግሉ መረጃዎችን በአግባቡ የሚይዙበት እና ስራ ላይ የሚያውሉበት የመረጃ አያያዝ ስርአት መዘርጋታቸውን በተመለከተ</u>

126. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር የሚያገለግሉ መረጃዎችን በአግባቡ  የሚይዙበት እና ስራ ላይ የሚያውሉበት የመረጃ አያያዝ ስርአት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

127. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ ህዝቦችና በአዲስ አበባ መስተደድር ስር በሚገኙ ተቋማትና ኮሌጆች ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር የሚያገለግሉ መረጃዎችን የሚይዙበትና ስራ ላይ የሚያውሉበት የመረጃ አያያዝ ስርዓት በተለያየ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል፡፡

128. በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ የነቀምት፣ ጅማና ደበና ኮሌጆች የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሲኖራቸው  የአምቦ እና ጊምቢ ተቋማት በተቋማቶቹ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ በተጠናከረ መልኩ ባለመሰራቱ ለቴክኖሎጅ ክምችትና ሽግግር

የሚያገለግሉ መረጃዎችን በአግባቡ የሚይዙበት እና ስራ ላይ የሚያውሉበት የመረጃ አያያዝ ስርአት አለመኖሩን ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡

129. በአማራ ክልል ከሚገኙ ተቋማት ውሰጥ አዲስ ዘመን፣ ደብረ ማርቆስና ዱርቤቴ ተቋማትና ኮሌጆች የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሲኖራቸው በሌላ በኩል የደጀን፣ ደንበጫ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ዳንግላ፡ አዴት እና እንጅባራ ተቋማት የመረጃ አያያዝ ስርዓት እንደሌላቸው ታውቋል፡፡ የመረጃ አያያዝ ስርአት ያልኖረበት ምክንያት የግንዛቤ እጥረት፣ በክህሎት ማነስና የተደራጀ የሰው ሀይልና ለስራው የሚያስፈልገው ቁሳቁስ ባለመኖሩ በተቋማቶቹ እንዳልተሠራ ገልፀዋል፡፡

130. በቦንጋ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ለቴክኖሎጂ ሽግግር ራሱን የቻለ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ሲኖረው፣ በቴፒ ቴክኒክና ሙያ ተቋም ግን ባለሙያ ባለመኖሩና በተቋሙ በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ ምንም አይነት ስራ ስላልተሰራ የመረጃ አያያዝ ስርአት እንዳልተዘረጋ የተቋሙ የስራ ኃላፊ ገልፀዋል፡፡

131. በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙት ብርሃነ ኢትዮጵያ እና ከፍተኛ 20 ቴክኒክና ሙያ ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ በተሰሩና ወደፊት ስለሚሰሩ ስራዎች ራሱን የቻለ የመረጃ አያያዝ ስርዓት እንዳላቸው ታውቋል፡፡ በሌላ መልኩ በአቃቂና ከፍተኛ 12 ቴክኒክና ሙያ ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ ምንም አይነት ስራ ያልተሰራ ሲሆን የመረጃ አያያዝ ስርአትም እንዳልተዘረጋ የኦዲት ቡድኑ ለተቋሙ የስራ ሀላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

132. ለአማራና ኦሮሚያ ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች ጉዳዩን በተመለከተ በቀረበው ቃለ መጠይቅ እና በተደረገው የመረጃ ክለሳ በክልል ቢሮ ደረጃ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በተጠናከረ መልኩ ቢኖርም በተቋማትና ኮሌጆች በኩል ያለው የመረጃ አያያዝ ስርዓት በተለይ በተቋማት የተደራጀ የሰው ሀይልና የቢሮ አደረጃጀት ባለመኖሩ ምክንያት ስራው ደካማ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

133. ለአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ ጉዳዩን በተመለከተ በቀረበው ቃለ መጠይቅ በኤጀንሲ ደረጃ ያለው የመረጃ አያያዝ ስርዓት በሀርድ ኮፒ ብቻ መሆኑንና ኃላ ቀር እንደሆነና የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ በተጠናከረ መልኩ አለ ማለት እንደማይቻል ገልጸዋል፡፡

134. ጉዳዩን በተመለከተ በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊ የኦዲት ቡድኑ ባቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ዌብ ሳይት፣ ዳታ ቤዝ፣ ዳታ ባንክ እና ሲዲ ወይም ዲቨዲ ለማዘጋጀት በአማራጭነት ተይዞ ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ዳታ ባንክን በፌደራል ደረጃ ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑንና የመረጃ ባንኩም በሁሉም ተቋማት ፣ ኮሌጆችና ክልሎች እንዲሁም የደረሰ ቢሆንም የመረጃ አጠቃቀም ብቃት ማነስ፣ አሰልጣኞች መረጃዎችን በአግባቡ አደራጅተው በባንኩ አለማስገባትና የክልል አስፈጻሚ አካላት በመረጃ ልውውጥ ሂደቱ ያላቸው ብቃትና ቁርጠኝነት አናሳ በመሆኑ ስራው በተፈለገው መጠን እየተሰራበት እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡

135. የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የመረጃ ክለሳ በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ ቀልጣፋ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት ባለመኖሩ ስራውን ለሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ሁሉ የሚያስተዋውቅ በቂ የመረጃ ፍሰት አለመኖሩን ከ2001 በጀት አመት የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ተገልጿል፡፡

136. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ለቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያስፈልጉ መረጃዎችን የሚያሰባስቡበት፣ የሚያደራጁበትና ስራ ላይ የሚያውሉበት የመረጃ አያያዝ ስርዓት በሰው ኃይልና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች በማሟላት በሁለቱም ተቋማት በተጠናከረ ሁኔታ አለመዘርጋቱ በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚጠበቀውን ውጤት ለማግኘት አስቸጋሪ ሊያደርገው ይችላል፡፡

## <u>በቴክኖሎጂ ማምረት ሂደት ወቅት የወጡ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን መመዝገባቸውን በተመለከተ</u>

137. በቴክኖሎጂ ማምረት ሂደት ወቅት የወጡ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን ተቋማትና ኮሌጆች በመመዝገብና በመተንተን አሠራራቸው ኢኮኖሚያውና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡

138. በናሙና በተመረጡ ከኦሮሚያ፣አማራ፣ ደቡብና አዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ውስጥ ጅማ፣ ቦንጋ፣ ቴፒ፣ ደበና፣ ነቀምት፣ ጊምቢ፣ አምቦ፣ ደጀን፣ ደብረ ማርቆስ፣ ደንበጫ ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ዳንግላ፣ እንጅባራ፣ ዱርቤቴ፣ አዲስ ዘመን፣ አዴት፣ ከፍተኛ 12፣ ከፍተኛ 20፣ አቃቂና ብርሃን ኢትዮጵያ ተቋማትና ኮሌጆች

በቴክኖሎጂ ማምረት ሂደት ወቅት የወጡ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን መዝግበውና ተንትነው እንደማያስቀምጡ ለኦዲት ቡድኑ ገልፀዋል፡፡ ስራውን ያላከናወኑበት ምክንያት በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ስለአሠራሩ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው በመሆኑ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

139. ጉዳዩን በተመለከተ በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊ የኦዲት ቡድኑ ባቀረበው ቃለ መጠይቅ ስራው የሚሰራው ምንም እንኳ ቴክኖሎጂዎቹን በሚሰሩ አካላት ቢሆንም በቴክኖሎጂ ማምረት ሂደት ወቅት የወጡ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን እንዴት መመዝገብ እንዳለባቸው በአሰራር ማንዋሉ ወይም ቱል ኪት መሰረት ማከናወን እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

140. በቴክኖሎጂ ማምረት ሂደት ወቅት የወጡ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን ቴክኖሎጂውን ያመረተው ተቋም ባለመመዝገቡና ተንትኖ ባለማስቀመጡ ቴክኖሎጂው የፈጀውን የዋጋ መጠን፣ የቴክኖሎጂውን አዋጭነትና ከዚህ በፊት ቴክኖሎጂው ከውጭ ሀገር የሚገባ ከሆነ ያስቀረውን የውጭ ምንዛሬ እንዳይታወቅ እና ለቀጣይ ስራዎች የሚያስፈልገውን በጀት በተጨባጭ መረጃ ተመስርቶ ለማዘጋጀት አያስችልም፡፡

## የቴክኖሎጅ ሽግግር ቅንጅታዊ አሠራርን በተመለከተ

141. የቴክኖሎጅ ሽግግር ስራን የማሰልጠኛ ተቋማት ከአሰልጣኞች፣ ከሰልጣኞችና ከአካባቢው ኢንዱስትሪ ጋር በመቀናጀት መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

142. በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ህዝቦችና በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራን ከአሰልጣኞች፣ ከሠልጣኞችና ከአካባቢው ኢንዱስትሪ ጋር በመቀናጀት የሚያካሄዱት ስራ የተለያየ የአፈጻጸም ደረጃ እንዳለው ለማወቅ ተችሏል፡፡

143. ከኦሮሚያ፣አማራ፣ ደቡብና አዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ውስጥ  ደብረ ማርቆስ፣ እንጅባራ፣ አዲስ ዘመን፣ዱርቤቴ፣ጅማ፣ቦንጋ፣ነቀምት፣ ከፍተኛ 12 እና ብርሃነ ኢትዮጵያ ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ የሚሰሩዋቸውን ስራዎች ከአሰልጣኞች፣ ከሰልጣኞችና ከአካባቢው ኢንዱስትሪ ጋር በመተባበር ወይም በመቀናጀት እንደሚሰሩ ታውቋል፡፡ በሌላ መልኩ በደንበጫ፣ አዴት፣

ፍኖተ ሰላም፣ ዳንግላ፣ ደጀን፣ ቴፒ፣ ከፍተኛ20፣ አቃቂ፣ አምቦ ደበና ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራን ከአሰልጣኞች ከሰልጣኞችና ከአካባቢም ኢንዱስትሪ ጋር በመቀናጀት እንደማይሰሩ ታውቋል፡፡ ስራው ያልተሠራበት ዋናው ምክንያት አሰልጣኝ መምህሩ ከማሰልጠን ስራው ጎን ለጎን እንዲሰራ በመደረጉ ስራውን እንደተጨማሪ ስራ አድርጎ የመውሰድ ችግር በመኖሩ በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ የሚሰሩዋቸውን ስራዎች ከጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ውጭ ከአሰልጣኞች፣ ከሰልጣኞችና ከአካባቢው ኢንዱስትሪ ጋር በመቀናጀት እንደማይሰሩ በኦዲት ቡድኑ ለሀላፊዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

144. ጉዳዩን በተመለከተ ለአማራ፣ ለኦሮሚያ እና ለአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ ስራው በተለይ በነባር ተቋማትና ኮሌጆች በተጠናከረ መልኩ እየተሰራ ቢሆንም በአዳዲስ ተቋማት በኩል ስራው ገና ጅምር ስለሆነና ስራውን ለመስራትም የተደራጀ የሰው ሀይልና በቂ ክህሎት ያለው ባለሙያ በማስፈለጉ ስራው በአጥጋቢ ሁኔታ እየተሰራ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

145. የኦዲት ቡድኑ ባካሄደው የመረጃ ክለሳ የቴክኖሎጂ ዝርዝር ንድፎችን አንብቦ ወደ ስራ መተርጎም አለመቻል፣ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ከአካባቢው ኢንዱስትሪና ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ፍላጎት ጋር እንደማይጣጣም ከ2001 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ተገልጿል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች በተፈጠረው የግንኙነት መድረክ መሰረት ለስራው ፈጣን ምላሽ ያለመስጠትና ስራዎችን በጋራ ከመፈጸም ይልቅ በተናጠል እንደሚሰሩ በ2003 በጀት አመት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ተጠቅሷል፡፡

146. የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራን የማሰልጠኛ ተቋማት ከአሰልጣኞች፣ ከሰልጣኞችና ከአካባቢው ኢንዱስትሪ ጋር በመቀናጀት ሁሉም ተቋማት የማይሰሩ ከሆነ ተሰርተው የሚሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎች ለአካባቢው ህብረተሰብም ሆነ ለኢንዱስትሪው የሚፈለገውን አስተዋፅኦ ላያበረክቱ ይችላሉ፡፡

## <u>ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር ስራ የሚውሉ ማንዋሎችና መመሪያዎችን በተመለከተ፣</u>

147. የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር ስራ የሚውሉ ማንዋሎችና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎቹ በማስራጨት ተግባራዊነታቸውን መከታተል ይኖርበታል፡፡

148. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ከኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ህዝቦች አና የአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትና ኮሌጆች ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር ስራ የሚውሉ በዘርፉ የተዘጋጁ ማንዋሎችኛ መመሪያዎች ለተቋማትና ኮሌጆች የደረሳቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተላኩት ማንዋሎችና መመሪያዎችን ስራ ላይ ለማዋል በትምህርት ሚኒስቴር በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ባለሙያዎች የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ የተጠናከረ እንዳልሆነ የኦዲት ቡድኑ ለተቋማቶቹና ለኮሌጆች የስራ ሀላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

149. ጉዳዩን አስመልክቶ በትምህርት ሚኒስቴር ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር ስራ የሚውሉ ማንዋሎችና መመሪያዎች የክልሎችን አቅም ለመገንባት እንደሚላክና አፈፃፀሙም በጋራ በምክክር ስብሰባ እንደሚገመገም እንዲሁም በተመረጡ ክልሎች ላይ የሱፐርቪዥን ስራ የሚሰራ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ባለው የሰው ሀይል እጥረት፣ በወቅቱ በነበረው የተሽከርካሪ እጥረትና ለስራው የሚያስፈልጉ እንደ ካሜራ፣ ላፕቶፕ ያሉ መሳሪያዎች አለመኖር ስራው ከታች እስከ ላይ በተጠናከረ መልኩ ክትትል እንዳይደረግበት በምክንያትነት ገልፀዋል፡፡

150. ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር ስራ የሚውሉ ማንዋሎችና መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊነታቸውን በፌደራልና በክልል የቴክኒክና ሙያ ባለሙያዎች ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ካልተደረገ የተዘጋጁ ማንዋሎችና መመሪያዎች በቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ እንዲያስገኙ የሚጠበቀው ውጤት ላይሳካ ይችላል፡፡

## ተቋማትና ኮሌጆች  የደሰሳ ጥናት ስለማድረጋቸው የሚደረገውን ክትትል በተመለከተ

151. የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ በተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚሰሩ ስራዎች ከሀገሪቱ እና ከአካባቢው የልማት አቅጣጫ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እንዲያካሂዱ የዳሰሳ ጥናት መደረጉን  ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

152. በናሙና ተመርጠው በኦዲት ቡድኑ በመስክት ጉብኝት ወቅት ከታዩትና ለስራ ሀላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ  በደብረ ማርቆስ፣ እንጅባራ፣አዲስ ዘመን፣ ነቀምት፣ ከፍተኛ 20 እና ብርሃን ኢትዮጵያ ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚሰሩ ስራዎች  ከሀገሪቱ የልማት አቅጣጫ እና ከአካባቢው የልማት ቀጠናዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እንዲካሄድ ለማስቻል የዳሰሳ ጥናት እንደሚያደርጉ ታውቋል፡፡ በሌላ መልኩ በጊምቢ፣ ዱርቤቴ፣ አዴት፣  ከፍተኛ 12፣  አቃቂ፣ ጅማ፣ አምቦ፣ ደጀን፣ ቴፒ፣ ደበና፣ ደንበጫ፣  ፍኖተ ሰላም እና ዳንግላ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ኮሌጆች የዳሰሳ ጥናት እንደማያካሂዱ ታውቋል፡፡ በተጠቀሱት ተቋማት የደሰሳ ጥናት ያልተካሄደው በስራው የተሰማሩ ባለሙያዎችና መምህራን ለስራው ያላቸው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑና ስራውን እንደተጨማሪ ስራ አድርጎ የመውሰድ የግንዛቤ ችግር በመኖሩ እንደሆነ የተቋማት የስራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

153. ጉዳዩን በተመለከተ ለኦሮሚያ እና ለአማራ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የቢሮ ሀላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚሰሩ ስራዎች ከሀገሪቱ የልማት አቅጣጫ እና ከአካባቢው የልማት ቀጠናዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እንዲካሄድ የዳሰሳ ጥናት በክልል ደረጃ እንደሚያካሂዱ ነገር ግን በሁሉም ተቋማትና ኮሌጆች ስራው እንደማይሰራ የኦዲት ቡድኑ ለስራ ሀላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

154. ስለ ጉዳዩ በትምህርት ሚኒስቴር ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የቴክኖሎጅ ዳሰሳ ጥናት እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ አጥጋቢ ባልሆነ ሁኔታ ሲሰራ የቆየ ሲሆን ከ2003 ዓ.ም በኋላ ግን እያንዳንዱ ሴክተር መ/ቤት የሚሰሩ ስራዎችን በዝርዝር በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ላይ ስላስቀመጠ የቴክኖሎጂ

ዳሰሳ ጥናት ሳያስፈልግ ስራውን የጋራ እቅድ በማዘጋጀት መስራት እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡

155. በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚሰሩ ስራዎች ከሀገሪቱ እና ከአካባቢው የልማት አቅጣጫ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እንዲካሄድ የዳሰሳ ጥናት ካልተደረገና በየደረጃው ክትትል እና ድጋፍ የማይደረግ ከሆነ የሚሰሩ ስራዎች የአካባቢውን ወይም የህብረተሰቡን ፍላጎት ያማከሉ ስለማይሆን በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚሠራው ስራ የሚጠበቀውን ውጤት ላያስገኝ ይችላል፡፡

## የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት መካሄዱን በተመለከተ

156. በትምህርት ሚኒስቴር በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ፣ የክልል ቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች፣ የማሰልጠኛ ኮሌጆችና ተቋማት የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

157. በናሙና በተመረጡ በኦሮሚያ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን ስር በሚገኙ በጅማ፣ ደበና፣ ነቀምት፣ ጊምቢ እና አምቦ እንዲሁም በአማራ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ስር በሚገኙ ደጀን፣ ደንበጫ፣ ፍኖተ ሰላም፣ እንጅባራ፣ ዳንግላ፣ ዱርቤቴ፣ አዲስ ዘመን እና አዴት ኮሌጆችና ተቋማት የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት ላይ የግንዛቤ እጥረት በመኖሩ፣ ለስራው የሚመደቡት አስተባባሪዎች በየጊዜው ከቦታ ቦታ መቀያየራቸው እና ስራውን እንደመደበኛ ስራ አድርጎ ባለመሰራቱ የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት እንዳልተካሄደ የተቋማት እና ኮሌጆች ዲኖች፣ ርዕሰ መምህራንና የቴክኖሎጅ ሽግግር አስተባባሪዎች የኦዲት ቡድኑ ባቀረበው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

158. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ስር በሚገኙ የቦንጋ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ እና የቴፒ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ የተሰሩ ስራዎች ላይ በባለሙያ እጥረትና ለስራው በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩ ምክንያት የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት እንዳልተካሄደ የኮሌጁ ዲንና የተቋሙ ርዕሰ መምህር የኦዲት ቡድኑ ባቀረበው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

159. በናሙና በተመረጡ በአዲስ አበባ ስር በሚገኙ የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ውስጥ ከፍተኛ 20፣ ከፍተኛ 12፣ አቃቂ እና ብርሃን

ኢትዮጵያ እንዲሁም ከግል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች ውስጥ አዲስ አበባ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና ዩኒቨርሳል ቴክኖሎጂ ኮሌጅ በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ በተሰሩ ስራዎች ላይ በግንዛቤ እጥረት እና በተቋማቶቹ በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ የተሰሩ ስራዎች አነስተኛ በመሆኑ የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት እንደማያካሂዱ ገልጸዋል፡፡

160. ጉዳዩን በተመለከተ ለኦሮሚያና ለአማራ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የስራ ሀላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት ላይ በጊዜ እጥረት እና በሰው ሀይል እጥረት ምክንያት ጥናቱ እንዳልተካሄደ የስራ ሀላፊዎች ገልጸዋል፡፡

161. ለአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ጉዳዩን በተመለከተ የኦዲት ቡድኑ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት ለኤጀንሲው መመሪያው ከተላለፈ ገና ከ6ወር እስከ 8ወር ድረስ በመሆኑ ጥናቱ እንዳልተከናወነ ገልጸዋል፡፡

162. ጉዳዩን አስመልክቶ በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ዳይሬክቶሬት የስራ ኃላፊ የኦዲት ቡድኑ ባቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ የቴክኖሎጂ ፋይዳ ደሰሳ ጥናት በፌዴራል ደረጃ እንዳልተከናወነ ገልፀዋል፡፡ ጥናቱ ያልተከናወነበት ዋናው ምክንያት የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ ከጫፍ እስከ ጫፍ የሚሰራ በመሆኑና እስካሁንም ቴክኖሎጂዎች የማሸጋገሩ ስራ በክልሎች የሚሰራ በመሆኑ በተሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎች ላይ የፋይዳ ዳሰሳ ጥናት ለመስራት ቴክኖሎጂዎች በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለመረዳት የጊዜ ቆይታ ማስፈለጉ፣ በፌደራል ደረጃ ያሉትም ቢሆን ተባዝተው ወደ ህብረተሰቡ የተሰራጩበት ሁኔታ አለመኖር እና የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ምንም እንኳ 17 (አስራ ሰባት) የሰው ሀይል እንደሚያስፈልግ ቢያስቀምጥም ስራውን በአምስት የሰው ሀይል ብቻ እንዲሰራ በመደረጉ የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት ማጥናት እንዳልተቻለ ገልጸዋል፡፡

163. በተሰሩ ቴክኖሎጂዎች ላይ የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት በተቀናጀ መልኩ በፌዴራል፣ በክልል እና በማሰልጠኛ ተቋማት አለመሰራቱ የተሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎች በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ እና በተሰሩትም ይሁን ወደፊት በሚሰሩ ቴክኖሎጂዎች ላይ የተገኘውን ውጤት ለመገምገም አያስችልም፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

### ሀ. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተቋማት አቅም ግንባታና የሰልጣኞች ልማት የስራ አፈፃፀም በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን በተመለከተ፡፡

- በናሙና ተመርጠው በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳደር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስልጠና ፍላጎት ጥናት አለማጥናታቸውና ለየክልላቸዉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮዎች ሪፖርት የማያደርጉ መሆኑ፣

- የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናት በፌዴራል ደረጃ በአገር አቀፍ ጥናት ሲካሄድ በክልል ደረጃ ደግሞ ክልል አቀፍ ጥናት ይካሄዳል፡፡ በአማራ እና ኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናት ቢያካሄዱም በጥናቱ መሠረት ሥልጠና የማይሰጡ መሆኑ እና በአዲስ አበባ መስተደደር ሥር የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ደግሞ የሥራ ገበያ ፍላጎት ጥናት አለማካሄዳቸው፣

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና የአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሙያ ደረጃው በሚያዘው መሠረት በቂ የስልጠና መሣሪያዎች አለመሟላታቸው፣

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና የአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስራ ትብብር እና ግንኙነት (clustering) ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም የስራ አፈፃፀሙ ያልተጠናከረና ተቋሟቱ እርስ በርሳቸው በቅንጅት የሚሰሩበት የስምምነት ሰነድ የሌላቸው መሆኑ፣

- በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የአዲስ አበባ መስተዳድር እና ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ የልህቀትን ማዕከል (coc) ውጤትን መሰረት በማድረግ የውጤት ተኮር ስልጠና ያለበትን ደረጃ አለመገምገማቸው፣

- በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በአብዛኛዎቹ የማሰልጠኛ ተቋማት ሰልጣኞች ከስልጠና በኋላ የትና በምን ሰራ እንዳሉ የተጠናከረ የድህረ ገበያ ጥናት የማያከናውኑ መሆኑ፣

- በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና የአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት

ሰልጣኞች የስልጠና ጊዜያቸውን 70%ቱን በኢንደስትሪ ውስጥ የትብብር የተግባር ስልጠና ማካሄድ ቢጠበቅባቸውም በኢንደስትሪ እጥረትና የግንዛቤ እጥረት በመኖሩ ስራው በተሟላ መልኩ አለመተግበሩ፣

- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ እና የክልል የቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በተጠናከረ መልኩ አለመደገፉ፣

## ለ. የቴክኖሎጅ አቅም ክምችትና ሽግግር ስርዓት ኢኮኖሚያዊና ብቃት ባለው መልኩ መከናወኑን በተመለከተ

- በኦዲት ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት አብዛኞቹ ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚሰሩ ስራዎች ከሀገሪቱ እና ከአካባቢው የልማት አቅጣጫ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እንዲካሄድ የተጠናከረ የቴክኖሎጂ ፋይዳ የዳሰሳ ጥናት እያደረጉ አለመሆኑ፣
- የምርጥ ቴክኖሎጂ ፍላጎት የመለየት፣ የመምረጥ፣ እና ቴክኖሎጂዎች እንዲሸጋገሩ መረጃውን ወደ ተቋማትና ኮሌጆች የመላኩ ስራ ከፌዴራል እስከ ተቋማት ድረስ በመቀናጀት በተጠናከረ መልኩ አለመሰራቱ እና በፌዴራል አና በክልል የቴክኒክ እና ሙያ ባለሙያዎች በሁሉም ተቋማት በቂ ክትትልና ድጋፍ አለመደረጉ፣
- የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ ከጫፍ እስከ ጫፍ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመስራት፣ እና ስራውን በባለቤትንት እንዲሰሩ ለሁሉም ተቋማት እና ኮሌጆች በዘርፉ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ አለመሰጠቱ፣
- በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኞዎቹ የማሰልጠኛ ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት የማያገለግሉ ሲሆን በክልሎች የቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች የሚደረገው ክትትል እና ድጋፍም አናሳ መሆኑ፣
- በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛ ዎቹ ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ የሚሰሩ ስራዎች ላይ የአካባቢውን የትኩረት ኢንደስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና እየሰሩ አለመሆኑ፣
- በናሙና ተመርጠው ከታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ ተቋማትና ኮሌጆች ለቴክኖሎጅ ክምችትና ሽግግር የሚያገለግሉ መረጃዎችን በአግባቡ የሚይዙበት እና ስራ ላይ የሚያውሉበት የመረጃ አያያዝ ስርአት ያልዘረጉና ስራ ላይ ያልዋሉ መሆኑ፣

- በናሙና ተመርጠው ከታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ የማሰልጠኛ ተቋማት እና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ማምረት ሂደት ወቅት የወጡ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን መዝግበውና ተንትነው አለመያዛቸው፣

- በናሙና ተመርጠው ከታዩት የአማራ፣ የኦሮሚያና የአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ አብዛኛዎቹ ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ የሚሰሩዋቸውን ስራዎች ከአሰልጣኞች፣ ከሰልጣኞችና ከአካባቢው ኢንደስትሪ ጋር በጋራ ለመስራት ቅንጅታዊ አሰራር የሌላቸው መሆኑ፣

- ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር ስራ የሚረዱ ማንዋሎችና መመሪያዎች በናሙና ተመርጠው ከታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር በሚገኙ ተቋማትና ኮሌጆች ቢደርሳቸውም መመሪያዎቹ በትክክል ስለመፈጸማቸው በፌደራልም ሆነ በክልልከ የቴክኒክና ሙያ ቢሮ ኃላፊዎች የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ አናሳ መሆኑ፣

- በናሙና ተመርጠው ከታዩት በአማራ፣ በኦሮሚያና በአዲስ አበባ መስተዳድር ስር የሚገኙ ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ሽግግር ለተሰሩ ስራዎች የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት ያላካሄዱ መሆኑ ታውቋል፡፡

ይህም የሚያሳየው በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፍ፣ በክልል ቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች እና በማሠልጠኛ ተቋማትና ኮሌጆች በውጤት ተኮር ስልጠናና በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ ከላይ የተገለጹት ድክመቶች መኖራቸው ነው፡፡ ስለሆነም ከላይ የተመለከቱትን ድክመቶች ለማሻሻል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሣቦች በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሀሳብ

## ሀ. በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተቋማት አቅም ግንባታና የሰልጣኞች ልማት የስራ አፈፃፀም በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን በተመለከተ፡፡

- የፌደራል እና የክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስልጠና ፍላጎት ጥናት እንዲያካሂዱ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- የፌደራልና የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና የስራ ገበያው ለሚፈልገው ክህሎትና የብቃት ደረጃ መልስ የሚሰጥ እንዲሆን በገበያ ጥናቱ መሰረት እንዲሰጥ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- የክልል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ቢሮዎች የአገር አቀፍ ሙያ ደረጃን የሚያሟላ ስልጠና ለመስጠት በተቋማቶቹ የተሟላ የስልጠና መስጫ መሳሪያዎች እንዲኖራቸው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- የክልል የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ቢሮዎች የማሰልጠኛ ተቋማት እርስ በርሳቸው በትብብር የሚሰሩበት (clustering) ስርዓት እንዲዘረጉና የስምምነት ሰነድ አዘጋጅተው ስራ ላይ እንዲያውሉ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ እና የክልል ቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች የልህቀት ማእከል (coc) ውጤትን መሰረት በማድረግ የውጤት ተኮር ስልጠና ያለበትን ደረጃ ከየተቋማቱ መረጃውን በማሰባሰብ እና በማጠናቀር መገምገም ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሰልጥነው የተመረቁ ሰልጣኞች ከስልጠና በኃላ የትና በምን ስራ ላይ እንዳሉ የድህረ ገበያ ጥናት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሰልጣኞች የስልጠና ጊዜያቸውን 70% በኢንደስትሪ ውስጥ በተግባር ስልጠና 30% ደግሞ በንድፈ ሃሣብ እንዲሰለጥኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ እና የክልል የቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተደግፎ እንዲሰጥ አስፈላጊውን ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## ለ. የቴክኖሎጅ አቅም ክምችትና ሽግግር ስርዓት ኢኮኖሚያዊና በብቃት መከናወኑን በተመለከተ

- በትምህርት ሚኒስቴር ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ እና በክልሎች የቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች ለተቋማትና ኮሌጆች ቴክኖሎጅዎች የምርጥ፣ የቴክኖሎጂ ፍላጎት የመለየት እና የማከማቸት ስርአት በመዘርጋት ቴክኖሎጂዎች በተፈለገው መጠን እንዲሸጋገሩና ውጤታማ ለማድረግ የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ መጠናከር ይኖርበታል ፡፡

- የፌደራሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ እና የክልል ቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር አሰራር ላይ የሚሰራው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በተጠናከረ መልኩ ሊሰሩ ይገባል፡፡

- በክልል የቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች የማሰልጠኛ ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል ሆነው ማገልገላቸውን በተመለከተ የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ በተጠናከረ መልኩ ሊካሄድ ይገባል፡፡

- ሁሉም የማሰልጠኛ ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ ስለሚሰሩዋቸው ስራዎች የአካባቢውን የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ሁሉም የማሰልጠኛ ተቋማት ለቴክኖሎጅ ክምችትና ሽግግር የሚያገለግሉ መረጃዎችን በአግባቡ የሚይዙበት እና ስራ ላይ የሚያውሉበት የመረጃ አያያዝ ስርአት/መዘርጋትና ስራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል፡፡

- በቴክኖሎጂ ሽግግር ስራ ሁሉም ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ማምረት ሂደት ወቅት የወጡ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን መመዝገብና መተንተን ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ተቋማትና ኮሌጆች በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ የሚሰሩዋቸውን ስራዎች ከአሰልጣኞች፣ ከሰልጣኞችና ከአካባቢው ኢንዱስትሪ ጋር በጋራ በቅንጅት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ እና የክልል የቴክኒክና ሙያ ቢሮዎች ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር ስራ የሚያግዙ ማንዋሎችና

መመሪያዎችን ለተቋማትና ኮሌጆች ከመላክ ባሻገር መመሪያዎቹ በትክክል ስራ ላይ ስለመዋላቸው መከታተል ይጠበቅባቸዋል፡፡

- በፌደራልና በክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮዎች ሁሉም የማሰልጠኛ ተቋማትና ኮሌጆች ቴክኖሎጂን ለማሸጋገር የሚሰሩ ስራዎች ከሀገሪቱ የልማት አቅጣጫ እና ከአካባቢው የልማት ቀጠናዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እንዲካሄድ ለማስቻል የዳሰሳ ጥናትና ማድረጋቸውን ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ሁሉም የቴክኒክና ሙያ ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ለተሰሩ ስራዎች ቴክኖሎጂው ያለበትን የብቃት ደረጃና ያስገኘውን ጥቅም በሚመለከት የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት መጠናቱን በክልልና እና በፌደራል ደረጃ ያለው የቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ ሊከታተልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲት ወቅት በትምህርት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች፣ የክልል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ቢሮ ኃላፊዎች እንዲሁም በናሙና ተመርጠው የታዩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ኮሌጆች የስራ ኃላፊዎች ላደረጉልን ከፍተኛ የስራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1

### የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
### <u>የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች</u>

የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡- <u>በትምህርት ሚኒስቴር የቴ/ሙ/ት/ስ/ ዘርፍ</u>

| ተ.ቁ | የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች<br>Audit Issues | የኦዲት መስፈርቶች<br>Evaluation Criteria |
|---|---|---|
| 1 | **በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተቋማት አቅም ግንባታና የሰልጣኞች ልማት የስራ አፈፃፀም መገምገም፡፡** | |
| | 1.1. የተቋማት አቅም ግንባታ ስራ በብቃት መከናዎኑን መገምገም | 1.1.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተቋማትን አቅም ለማሳደግ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ሀብት /ሪሶርስ/በማፈላለግ ለተቋማቱ እንዲዳረስ ማድረግ ይኖርበታል፡፡<br><br>ምንጭ፡ ስትራቴጅ 41 |
| | | 1.2.የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ በተቋማት ውስጥ ያለውን ውስን ሀብት በቁጠባ እንዲጠቀሙ የሚያስችል መመሪያ ማዘጋጀትና ተግባራዊነቱን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡<br><br>ምንጭ፡ ስትራቴጅ 41 |
| | | 1.3.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የስልጠና ፍላጎት በማጥናት ለክልል የቴክኒክና ሙያ አስፈጻሚ አካላት በየአመቱ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡<br><br>ምንጭ፡ ስትራቴጅ 40 |
| | | 1.4.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና የስራ ገበያው ለሚፈልገው ክህሎትና የብቃት ደረጃ መልስ የሚሰጥ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡<br><br>ምንጭ፡ ስትራቴጅ 7 |
| | | 1.5.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የማሰልጠኛ ተቋማት የሚመሩበትና እውቅና የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚወስኑ መመሪያዎችን ማውጣትና አፈፃፀማቸውን መከታተል ይኖርበታል፡፡<br><br>ምንጭ፡ አዋጅ |
| | | 1.6. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ትልልቅ ኩባንያዎች፣ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ስራ ድርጅቶች ከተቋማት ጋር |

| | | |
|---|---|---|
| | | እንዲተባበሩና የስራ ላይ ስልጠና ለመስጠት እንዲችሉ የማበረታቻ መንገዶች መቀየስ ይጠበቅበታል፡፡<br><br>ምንጭ፡ ስትራቴጅክ 37 |
| | | 1.7.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ በተቋማት የሚሰጠው ስልጠና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ለመደገፍ የሚያስችል ስልት በመቀየስ ተግባራዊነቱን መከታተል ይኖርበታል፡፡<br>ምንጭ፡፡ ስትራቴጂክ 41 |
| | | 1.8. የክልል ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲዎች የአገር አቀፍ ሙያ ደረጃን የሚያሟላ ስልጠና ለመስጠት በተቋማቶቹ የተሟላ የአገልግሎት መስጫ መሳሪያ አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡<br><br>ምንጭ፡ ስትራቴጂክ 41 |
| | | 1.9.የክልል የቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲዎች በስራቸው ለሚገኙ ተቋማት የስራ ትብብርና ግንኙነት (clustering) ስርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን መከታተል ይጠበቅባቸዋል፡፡<br>ምንጭ፡ effectiveness and efficiency in TVET 14 |
| | | 1.10. የክልል የቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲዎች የማሰልጠኛ ተቋማት እርስ በርሳቸው በቅንጅት የሚሰሩበት የስምምነት ሰነድ አዘጋጅተው ስራ ላይ ማዋላቸውን መቆጣጠር ይኖርባቸዋል፡፡<br>ምንጭ፡ effectiveness and efficiency in TVET 14 |
| | | 1.11.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ በፌደራል ደረጃ የዘርፉን ስራ የሚከታተልና የሚያስተባብር ካውንስል ሊያቋቁምና የሚጠበቅበትን የሰራ ድርሻ ማከናወኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡<br><br>ምንጭ፡ ስትራቴጅክ 38 |
| | 1.2 በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የሰልጣኞች ልማት እንቅስቃሴ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም | 1.2.1.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የህልቀት ማእከል (coc) ዉጤትን መሰረት በማድረግ የውጤት ተኮር ስልጠና ያለበትን ደረጃ መገምገም ይኖርበታል፡፡<br>ምርጥ ተሞክሮ |
| | | 1.2.2.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሰልጥነው የተመረቁ ሰልጣኞች ከስልጠና በኃላ የትና በምን ስራ ላይ እንዳሉ የድህረ ገበያ ጥናት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡<br>ምርጥ ተሞክሮ |
| | | 1.2.3.በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የሰልጣኞች ልማት ንዑስ የስራ ሂደት የስራ ገበያ ፍላጎት ዳሰሳ ስርዓት በመዘርጋት ሀገራዊ የስራ ገበያ ፍላጎት ጥናት ማከናወን ይኖርበታል፡፡<br>ምንጭ፡ ስትራቴጅክ 41 |
| | | 1.2.4.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ሴቶች ፣ አካል ጉዳተኞች እንዲሁም ታዳጊ ክልሎች ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ የሚያሰችል ስርዓት መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ምንጭ ፣አዋጅ |
| | | 1.2.5. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የስልጠና ፋይዳ ግምገማ ማንዋልና የመገምገሚያ መሳሪያ በማዘጋጀት አፈጻጸሙን መከታተል ይኖርበታል፡፡<br><br>ምንጭ፡ BPR |

| | | |
|---|---|---|
| | | 1.2.6. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሰልጣኞች የስልጠና ጊዜያቸውን 70% ቱን በኢንዱስትሪው 30% ቱን ደግሞ በተቋማት ውስጥ እንዲያሳልፉ ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ምንጭ፡በፌደራል ቴክኒክና ሙያ ት/ስ አዋጅ ማብራሪያ |
| | | 1.2.7.በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች የተደራጁ ሰራተኞች ያለባቸውን የሙያ ክፍተት በመለየት ስልጠና መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡<br><br>ምንጭ፡ 2003 እቅድ አፈጻጸም |
| 2 | **በቴክኒክና ሙያ የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ስርዓት መዘርጋቱን ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድና ብቃት ባለው ሁኔታ መከናወኑን መገምገም** | 2.1በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የቴክኖጂ ሽግግር ዋና የስራ ሂደት የቴክኖሎጂ ፋይዳ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ይኖርበታል ፡፡<br>ምንጭ BBR p 86 |
| | | 2.2 የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የምርጥ ቴክኖሎጂ ፍላጎት የመለየት፣ የመምረጥ እና የማከማቸት ስርአት በመዘርጋት ቴክኖሎጂዎች እንዲሸጋገሩ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡<br>ምንጭ BPR p88 |
| | | 2.3 የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለክልል ለቴክኒክና ሙያ አስፈጻሚ አካላት፣ ለቴ/ሙ/ስ ተቋማትና ለህብረተሰቡ በቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር አሰራር ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራወች መሰራት ይጠበቅበታል፡፡<br>ምንጭ 2003 እቅድ አፈጻጸም 61 |
| | | 2.4.የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች ተቋማት በቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከልነት ማገልገላቸውን መከታተል ይጠበቅባቸዋል፡፡<br>ምንጭ ስትራ ገጽ 42 |
| | | 2.5.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የአካባቢዉን የትኩረት ኢንዱስትሪ በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትንተና ስራ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡<br>ምንጭ ቴ፡/ሽ ማንዋል 17 |
| | | 2.6የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ለቴክኖሎጅ ክምችትና ሽግግር የሚያገለግሉ መረጃዎችን በአግባቡ የሚይዙበት እና ስራ ላይ የሚያውሉበት የመረጃ አያያዝ አስርአት ሊዘረጉ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡የቴ/ሽ ማንዋል 4 |
| | | 2.7. በቴክኖሎጂ ማምረት ሂደት ወቅት የወጡ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን ተቋማት ሊመዘገቡና ሊተነትኑ ይገባል፡፡<br>ምንጭ፡የቴክኖሎጅ ማንዋል<br>ገጽ 13 |
| | | 2.8.የቴክኖሎጅ ሽግግር ስራን የማሰልጠኛ ተቋማት ከአሰልጣኞች ፣ከሰልጣኞችና ከአካባቢው ኢንዱስትሪ ጋር በመቀናጀት መሰራት ይኖርባቸዋል፡፡<br>ምንጭ፡የቴክኖሎጅ ማንዋል<br>ገጽ 16 |

| | | |
|---|---|---|
| | | 2.9.የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ ለቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር ስራ የሚውሉ ማንዋሎችና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ተግባራዊነታቸውን መከታተል ይኖርበታል፡፡<br>ምንጭ፡የቴክኖሎጂ ማንዋል16 |
| | | 2.10 በክልል ደረጃ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ አስፈጻሚ አካላት በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙርያ የተሰሩ ስራዎችን ለፌደራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፍ በየስድስት ወሩ ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡<br><br>ምንጭ፡የቴክኖሎጅ ማንዋል 16 |
| | | 2.11የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ የስልጠና ፕሮግራሞቹ ከሀገሪቱ የልማት አቅጣጫ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እየተካሄዱ ስለመሆናቸው ጥናትና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡<br>ምንጭ፡ አዋጅ |